13 —

# መንፈስ ቅዱስ

# እና

# ካሪዝማዊ ቀውሶች

ከዘላለም መንግሥቱ

አሳታሚ ፦ የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን
የሥነጽሑፍ አገልግሎት
የመ.ሣ.ቁ 5829 አዲስ አበባ ፣ ኢትዮጵያ
Publisher :- Ethiopian kale Heywet Church
Literature Service
P.O.Box 5829 Addis Ababa,
Ethiopian
ኅዳር 1989
November 1996

መልሶ ለማሣተም መብቱ የደራሲው ነው ።

ስለዚህ መጽሐፍ ጥያቄ ወይም አስተያየት ካለዎት ለሚቀጥለው በዚህ በካራዝማዊ ቀውሶች ላይ በሰፊው ለሚጸፈው ጽሑፍ ስለሚረዳን በሚቀጥለው አድራሻ ጻፉልን ፦
ለመንፈስ ቅዱሳን ካሪዝማዊ ቀውሶች ደራሲ
የመ.ሣ.ቁ. 5829
አዲስ አበባ፦ ኢትዮጵያ

# መቅድም

የዚህ መጽሐፍ አሳብ የተጸነሰው በ1985 "የካሪዝማዊ ክርስትና ታሪክ" የተሰኘውን ትምህርት በመውሰድ ላይ ሳለሁ ነበር። በብዙ ረገድ ስፋት እንጂ ብዙም ጥልቀት የሌለው የአገራችን ክርስትናም ችግር እየታየኝ ጀመርኩት - መንፈስ ቅዱስንና ዓይነተኛውን መንፈሣዊ ሕይወት ልናውቅ ለምንወድ እንዲረዳን ብዬ፤ መንፈሣዊ በሚመስሉ ስሜታዊ (እና ምናልባትም ሰይጣናዊ) ንቅናቄዎች የሚናወጡትን ያረጋጋና የተወሰዱትንም ይመልስ እንደሆን ብዬ። ይህን ተስፋ ጨብጬ ነው የጻፍኩት።

ምዕራፍ አንድ በመንፈስ ቅዱስ ማንነት እና ስራዎቹ ላይ ያተኮረ ነው። እኛም ከርሱ ጋር ሊኖረን ስለሚገባን ግንኙነት መልክ ይናገራል። የምዕራፍ ሁለት አንጻሮት የጸጋ ስጦታዎች ዓላማና ምንነታቸው ነው። ያለብስለት አንዳንዶቹን እንደ ባንዲራ እናውለበልባቸዋለን። አንዳንዶቹን ደግሞ መኖራቸውንም አናውቅ። ቢሆንልን በተሰጠንና በተሰማራንበት እናፍራ፤ ባይሆን እንኳ ቢያንስ እንወቃቸው። ምዕራፍ ሦስት ታሪካዊ ይዘት አለው። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ እውነተኛ መንፈሣዊ መነቃቃቶችና ጤናማ የጸጋ ስጦታ አገልግሎቶች መኖራቸውን እናያለን። በዚህም ልክ ደግሞ የስህተት አሰራሮችና ልምምዶችም ጠፍተው ያለማወቃቸውን ገሃድነት እናነባለን። በምዕራፍ አራት ከእነዚህ የስህተት ልምምዶች፥ አሰራሮችና ትምህርቶች በርካታዎቹ ተቃኝተዋል። ጥቂቱን ቀንጭቤ በብዕር ስም በቃለ ሕይወት እና የምሥራች መጽሔቶች በመጣጥፍ መልክ አቅርቤ ተነበዋል፤ ምላሾችም ነበሯቸው። አሁን ደግሞ በሙሉ እነሆ።

ዘላለም መንግሥቱ

ሐምሌ 1988 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

## ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሜ ይህ ስራ ያሳሰበኝንና በሂደቱም የረዳኝን ጌታ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ። "ለእርሱ በቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ኢየሱስ እስከ ትውልዶች ሁሉ ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን። (ኤፌ.3:21)

አቶ አክሊሉ ሙላት፥ ዶ/ር ብራየን ፋርገር፥ መጋቢ ስብሐት ጠና፥ ዶ/ር ሙላቱ ባፋ፥ አቶ ጥላሁን ኃይሌ፥ አቶ ደምሴ ማዴ፥ አቶ ዓለማየሁ ደበበ፥ አቶ ዳምጠው እሸቴና አቶ ሰለሞን ኃይለ ኢየሱስ በማንበብና አስተያየታቸውን በመስጠት የማይደንቀውን ትብብር ስላደረጉ አመሰግናለሁ።

አቶ ወንድዬ አሊ ዋናውን ጽሑፍ በማረምና ቋንቋውን በመግራት እንዲሁም ወ/ት ሰብለ ሙላቱ የኮምፒዩተር ጽሑፉንና ዕርማቱን በትጋት በመስራት ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክተዋልና አመሰግናቸዋለሁ።

ሁሉንም ጌታ አብዝቶ ይባርካቸው። አሜን።

## አበርክቶት

ለባለቤቴ ለፀሐይ አሰፋ መታሠቢያ ይሆን ዘንድ በፍቅር አበረክታለሁ።

# ማውጫ


ገጽ

መቅድም ..........................................................................

መግቢያ ........................................................................... 1

ምዕራፍ አንድ፤ የመንፈስ ቅዱስ ማንነት .................................. 3

መንፈስ ቅዱስ ሰብነት ነው ..................................................... 8

የሚመሰልባቸው ምሳሌዎች ...................................................... 10

የመንፈስ ቅዱስ ተግባራት (ብ.ኪ.) ........................................... 15

የመንፈስ ቅዱስ ተግባራት (አ.ኪ.) ........................................... 16

የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ......................................................... 21

የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ............................................................ 29

የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በአዲስ ኪዳን ...................................... 42

በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚፈጸሙ ኃጢአቶች ............................... 45

ምዕራፍ ሁለት፤ የጸጋ ስጦታዎች ............................................ 51

የጸጋ ስጦታ የተገለጠባቸው ቃላት ........................................... 51

የጸጋ ስጦታዎች ምንነትና ዓላማ ............................................ 56

አማኞች ሁሉ ስጦታ(ዎች) ተሰጥቷቸዋል ................................. 60

የጸጋ ስጦታዎች ዝርዝር በአዲስ ኪዳን ................................... 62

ገጽ


የጸጋ ስጦታዎች በቀረቤታ ዕይታ .................................... 64

የጸጋ ስጦታን ማወቅ .................................... 97

ምዕራፍ ሦስት ፤ ካሪዝማዊ መነቃቃቶችና እንቅስቃሴዎች

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ .................... 118

ምዕራፍ አራት፤ ካሪዝማዊ ቀውሶች .................................... 145

በመንፈስ መገንደስ .................................... 151

"የቀባኋቸውን አትዳስሱ" .................................... 162

ፊደልና መንፈስ፥ ቃልና ኃይል? .................................... 170

የመገለጥና የጭንቅላት ዕውቀት .................................... 173

እባብ ያገኙ ቹና መርዝ ጠጪዎቹ .................................... 180

ቃል-እምነት .................................... 184

የአምልኮ ቀውስ .................................... 189

የእምነት ቀውስ .................................... 193

የልሳኖች ቀውስ .................................... 198

የፈውስ ቀውስ .................................... 212

የተአምራት ቀውስ ("ሦስተኛው ሞገድ") .................................... 225

የሐብት ቀውስ .................................... 228

አዲሱ ቀውስ ('ቅዱስ' ሳቅ) .................................... 236

# መግቢያ

እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ሁሉ የሰጠው ለድንቅነቱ ወሰን የሌለው ስጦታ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሕይወት የሚገኘው በዚህ አንድ መንገድ ማለትም በክርስቶስ ብቻ ነው። የአንድ ሰው የክርስቲያንነቱ ምልክትና መታወቂያ የክርስቶስ ህልውና በርሱ ውስጥ መኖሩ ነው። የሕይወት ምንጭ ክርስቶስ ያልኖረበት ማንም ሰው ክርስቲያን አይደለም ሕይወትም የለውም። "ልጁ ያለው ሕይወት አለው የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም።" (1ዮሐ.5:12) አንድ ሰው ክርስቲያን የሚሆነው በዕውቀትና በእምነት ውሳኔ ላይ በተመሠረተ ግንኙነት አማካይነት ነው። ያም ጌታን እንደ ግል አዳኝ አድርጎ መቀበል ነው። አንድ ሰው ጌታን በሚቀበልበት ቅጽበት በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ዳግም ይወለዳል የእግዚአብሔርም ልጅ ይሆናል። (ዮሐ.3:5 እና 1:12-13) ከዚያችም ቅጽበት ጀምሮ ያ አማኝ የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ወይም ማደሪያ ይሆናል።

ዳግም መወለድና ከፍጥረታዊ ሰውነት ወደ ክርስቶስ ሕይወት ውስጥ መግባት ድንቅ ልምምድ ቢሆንም አንድ ሰው ክርስቲያን ከሆነ በኋላ ስጋዊ ወይም መንፈሳዊ ሆኖ የመኖር ሁለት ምርጫዎች ይገጥሙታል። ስጋዊ ክርስትና ክርስቲያን ከሆኑም በኋላ እንደ ማንኛውም ሰው መመላለስና በመንፈስ ያለማደግ ሲሆን ይህ ጌታን የማያስከብር ሕይወት ነው። እግዚአብሔር ሁሉም ልጆቹ መንፈሳውያን እንዲሆኑ ይፈልጋል። መንፈሳዊነት ማለት በአጭሩ ክርስቶስን የሚመስልና ለመምሰልም ቀን በቀን የሚጥር ሕይወት ነው። ማንም ክርስቲያን ፍጹም አይደለም ወደ ፍጹምነት የሚያድግ እንጂ። የክርስቶስን ባህርይ በአማኝ ሕይወት ውስጥ እንዲታይ የሚያደርገው መንፈስ ቅዱስ ነው። እውነተኛ መንፈሳዊነት የሚገኘው በመንፈስ ቅዱስ በመመራትና ራስን ለመንፈስ ቅዱስ በማስገዛት ነው። ስለዚህ አንድ ክርስቲያን ከዳግም ልደቱ ጀምሮ የሰመረ ሕይወትና አሸናፊ ኑሮ ለመኖር ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የተጣጣመ ግንኙነት ሊኖረው ይገባል። ይህ ግንኙነት ደግሞ የየዕለቱ ግንኙነት ነው እንጂ በአንድ ወቅት ብቻ የሚኖር ወይም የተደረገ ልምምድ ወይም እንደ ታሪክ የሚነገር የአንድ ወቅት ገጠመኝ ብቻ አይደለም።

ይህ የተጣጣመ ግንኙነት ደግሞ የመንፈስ ቅዱስን ማንነት ከማወቅና ስራውንም ከመረዳት የሚመነጭ ነው። በዚህ መጽሐፍ የመንፈስ ቅዱስን ማንነትና ሥራውን፥ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የታዩ የጸጋ ስጦታ (ወይም ካሪዝማዊ) መንቀሳቀሶችን የጸጋ ስጦታዎችን ምንነትና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚሰጡትን ገንቢ አገልግሎት እንዲሁም በመንፈስ ቅዱስ ወይም በመንፈሳዊ

መነቃቃትና ንቅናቄዎች ስም የተደረጉና የሚደረጉ የተቃወሱና መስመር የሳቱ ልምምዶችን ለመዳሰስ ጥረት ተደርጓል። የመጽሐፉ ዓላማ እነዚህን ነገሮች በመረዳት ለመንፈስ ቅዱስ ያለን አክብሮትና መስጠት እንዲያድግ የጸጋ ስጦታዎችን በመጠኑም ቢሆን በጥልቀት እንድንረዳ እንድናደንቅና ጤናማ በሆነ ሁኔታም እንድናገለግል እንዲሁም ከተቃወሱና መንፈሳዊ ከሚመስሉ የሃሰት አሰራሮች እንድንጠበቅ ለማስጠንቀቅ ነው።

ዘ. መ.

የካቲት 1986 ዓ.ም.

ቫንኩቨር፥ ካናዳ

# ምዕራፍ አንድ

# የመንፈስ ቅዱስ ማንነት

አንዳንድ ኃይማኖቶችና የስህተት ትምህርቶች መንፈስ ቅዱስን ተጽዕኖን ወይም አንድ አይነት አፅንዖትን ብቻ እንደሚያሳድር የሆነ ግዑዛዊ ጉልበት ወይም እንደ አንድ የሆነ ኃይል ብቻ አድርገው ያዩታል። ከነዚህ ትንሽ ሻል ያሉት ደግሞ መንፈስ ቅዱስን የአምላክ ቁራጭ ወይም ከእግዚአብሔር እንደሚወጣ የሆነ ግፊት ወይም ኃይል እንደሆነ ያያሉ ያስተምራሉም። በስህተት ትምህርቶች ዘንድ በአንዳንድ አባባሎችና በሚዘመሩ የመዝሙር ሐረጎች አማካይነት መንፈስ ቅዱስ ትክክለኛ መልኩና እውነተኛ ማንነቱ ተዛንፎ በአማኞች አዕምሮ እንዲቀረጽ ይደረጋል። ለምሳሌ መንፈስ ቅዱስ እንደ ደመና እንደ እሳት ወይም ሙቀት ወይም እንደ ድምጽ ተደርጎ ይዘመራል። እንደዚህ ከተዘመረና አንድ ቀን አንድ ዓይነት ምልክት ቢከሰት ምን ዓይነት መወናበድ እንደሚፈጠር መገመት ብቻ ምስሉን ሊያሳይ ይችላል። መዝሙሮች በሰዎች የሚደረሱ ናቸውና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርቶቻችንን በምንዘምራቸው መዝሙሮች ላይ ማስደገፍ አይኖርብንም። በእርግጥ መንፈስ ቅዱስ የሚመሰልባቸው ምስሎች አሉ። ይህ ማለት ግን መንፈስ ቅዱስ እነዚያን ነገሮች ነው ማለት አይደለም። መንፈስ ቅዱስ በርግብ ይመሰላል ማለት ርግብ ነው ማለት አይደለም። ልክ ጌታ ክርስቶስ "በግ" ሲባል ልንረዳው የሚገባን ምስሉን እንጂ የቤት እንስሳውን ነው ማለት አይደለም። ወይም እግዚአብሔር "በንስር ክንፍ ተሸከምኋችሁ" ሲል የሚበርረው አሞራ ሊመስለን አይገባም።

መጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስን እንደ ኃይል ወይም ጉልበት ግፊታዊ ወይም ስበታዊ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር የሆነ ነገር አድርጎ አያስተምርም። መንፈስ ቅዱስ የሆነ ነገር አይደለም። መንፈስ ቅዱስ አካል ወይም ሰብነት ነው፤ መንፈስ ቅዱስ አምላክ ነው። አካል ሲባል በአጭሩ ሰው ነው ማለት ሳይሆን አካላዊ ስብዕና ሊገልጧቸው በሚችሏቸው ባህርያትም ማንነቱ ይገለጣል ማለት ነው። አምላክ ነው ሲባልም በአጭሩ ከአብና ከወልድ ጋር እኩል የሆነ የማይተናነስ መለኮትነት ያለው የሥላሴ ሦስተኛ አካል ነው ማለት ነው። ሥላሴ ማለትም እግዚአብሔር ሦስት አማልክት ነው ማለት ሳይሆን አንድ ሆኖ በዚህ አንድ መለኮታዊ ኅልውና ውስጥ የሦስት አካላት መኖር ማለት ነው። እነዚህም አካላት አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ናቸው።

ሐዋርያው ጳውሎስ ወንጌልን እየሰበከ ወደ ኤፌሶን በመጣ ጊዜ አንዳንድ ደቀ መዛሙርትን አገኘና ባመኑ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን እንደተቀበሉ ሲጠይቃቸው እንኳን መቀበል መኖሩንም እንዳልሰሙ ነበር የነገሩት። መንፈስ

ቅዱስን ያለማወቅ እጅግ ከፉ ስህተት ነው፥ ለእርሱ ያለንን ግምት ያበላሸዋል የሚገባውን ክብር እንድንነሳውና ስራውንም እንዳንረዳ ያደርገናል። አውቀን ባንጨርሰውም ማንነቱን ማወቅ እና አውቆ መታዘዝ ደግሞ በአንጻሩ ድንቅ የሆነ ብፅዕና ነው።

መንፈስ ቅዱስ በብዙ መጠሪያዎች ይጠራል። ለምሳሌ፥

መንፈስ ቅዱስ (ሉቃ.4:1)፥

አጽናኝ ወይም ጰራቅሊጦስ (ዮሐ.14:26)፥

የእውነት መንፈስ (ዮሐ.16:13)፥

አብ የሰጠው የተስፋ ቃል (ሐዋ.1:5)፥

የሕይወት መንፈስ (ሮሜ.8:2)፥

የቅድስና መንፈስ (ሮሜ.1:4)፥

የክርስቶስ መንፈስ (ሮሜ.8:9)፥

የልጅነት (ልጆች የሆንንበት) መንፈስ (ሮሜ.8:15)፥

የእግዚአብሔር መንፈስ (1ቆሮ.3:16)፥

የፍቅር የኃይልና ራስን የመግዛት መንፈስ (2ጢሞ.1:7)፥

የዘላለም መንፈስ (ዕብ.9:14)፥

የጸጋው መንፈስ (ዕብ.10:29) በመባልም ይጠራል።

መንፈስ ቅዱስ የቅድስት ሥላሴ ሦስተኛ አካል ነው። እግዚአብሔር አምላክ አንድ አምላክ ሆኖ በሦስት አካላት የተገለጠ አንድ አምላክ ነው። አካላቱም አብ፥ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ ናቸው። "ሥላሴ" የሚለውን ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባናገኘውም ኀልውናው ግን በግልጽ ተጽፎልናል። ቃሉን የፈጠረልን ጠርጡልያኖስ የተባለ በ2ኛው ምዕተ ዓመት የኖረ የቤተ ክርስቲያን አስተማሪ ነው። ሥላሴ የሚለውን ቃል በጽሑፍ ደረጃ መጀመሪያ

የተጠቀመው የአንጾኪያው ቴዎፍሎስ እንደሆነ ይገመታል።[1] እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው። (ዘዳ.6:4) የዚህ አንድ አምላክ ሦስት አካላት በግልጽ በአዲስ ኪዳን ይታይ እንጂ በብሉይ ኪዳንም የኅልውናው ማስረጃ ይገኛል። ለምሳሌ በዘፍ.1:1 'እግዚአብሔር' የሚለው ቃል የነጠላ ሳይሆን በዕብራይስጥ የብዙ ስም ነው ከባለቤቱ ጋር የተያያዘው 'ፈጠረ' የሚለው ግስ ግን ነጠላ ነው። እዚያው ምዕራፍ ቁጥር 26 ላይ 'እግዚአብሔር'= ብዙ፤ 'አለ'= ነጠላ፤ 'እንፍጠር'= ብዙ። በሰዋሰው ሕግ ባለቤትና ግስ መዛመድ አለባቸው እዚህ ግን የሚፋለስ ይመስላል። እውነቱ ግን መፋለሱ ሳይሆን የሥላሴ ኅልውና መግለጫ መሆኑ ነው።

በአዲስ ኪዳን እግዚአብሔር ሥላሴ መሆኑ ቁልጭ ብሎ ይታያል። በማቴ.3:16-17 ጌታ በተጠመቀ ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ በእርሱ ላይ መውረድና የአብ ደግሞ መናገር በግልጽ ተጽፎአል። ጌታ ኢየሱስም ከትንሳኤው በኋላ ሐዋርያቱን ሲልካቸው በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እንዲያጠምቁ ነው የነገራቸው። (ማቴ.28:19-20) በተጨማሪም ዮሐ.14:16 እና 26 እንዲሁም 2ቆሮ.13:14 ተመሳሳይ እውነት ያስተምሩናል። እንዲህ ከሆነ እግዚአብሔር አብ አምላክ ነው እግዚአብሔር ወልድም አምላክ ነው በተመሳሳይ ሁኔታ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም ደግሞ አምላክ ነው።

## መንፈስ ቅዱስ አምላክ ነው

የመንፈስ ቅዱስን መለኮትነት መጽሐፍ ቅዱስ በማያወላዳ መንገድ ይነግረናል። መንፈስ ቅዱስ አምላክ መሆኑን የሚክዱ አንዳንድ የስህተት ትምህርቶች አሉ የይሆዋ ምስክሮች እንደ ምሳሌ ሊወሰዱ ይችላሉ። ዘመናዊዎቹ ምስክሮች የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት በሌላ ለመለወጥ እየጣሩ አባላትን ሲያጠምቁ 'በአብ፥ በወልድና መንፈስ ቅዱስ በሚመራው ድርጅት ስም' ብለው እስከማጥመቅ ደርሰዋል።[2] ይህ 'ድርጅት' የተባለው 'የዋችታወር የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር' የሚባለው መሆኑ ነው። እኒህ የስህተት አስተማሪዎች የመንፈስ ቅዱስን ሕልውና ዝቅ ከማድረጋቸውም ሌላ የእርሱን ስም ቦታና ክብር ለሰው ሰራሽ ድርጅታቸው ሰጥተዋል። እነዚህና ሌሎችም አንዳንድ የስህተት ትምህርቶች መንፈስ ቅዱስን እንደ አምላክ ሳይሆን በሰዎች አስተሳሰብና አመለካከት ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር ኃይል ብቻ አድርገው ይመለከቱታል። መንፈስ ቅዱስ አምላክ ነውና መለኮታዊ እርሱነቱን የሚቀንስ አንዳች የተዛነፈ አመለካከት ቢኖረን ወይም ይህን መሳይ ትምህርት ብንሰማ

ይህ ስህተት መሆኑን አንዘንጋ። ይህ ስህተት ደግሞ በአምላክ ኅልውና ላይ የተሰነዘረ በመሆኑ እንደ ቀላል የማይታይ ነው። ይህ የስህተት ትምህርት ገና በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመንና ከዚያም በፊት ነበር የተጀመረው። የዚህን ሐሳዊ ትምህርት ምንነትም ለመግለጥና ለመጠንቀቅም የአብያተ ክርስቲያናት አበው በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን (በ381 ዓ.ም.በቁስጥንጥንያ) ጉባዔ ተቀምጠው ነበር። ይህ ጉባኤ መንፈስ ቅዱስ አምላክ መሆኑን እርግጠኛ የሆኑበት፥ ብዙ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የተነሱ ትምህርቶች ምላሽ ያገኙበትና እነዚህ የስህተት አስተማሪዎችም የተወገዙበት ጉባኤ ነበር። ሌሎች ሐሳዊ ትምህርቶች ደግሞ የመንፈስ ቅዱስን ማንነት በትምህርት ደረጃ ተቀብለው ከእርሱ ጋር በሚኖረው ተግባራዊ ግንኙነት ግን ከእነዚያ ባልተሻለ መንገድ ያስተናግዱታል። አንዳንዶቹ ደግሞ ከሥላሴ አካላትም ሁሉ አብልጠው እርሱን ብቻ ያጎሉታል። ይህም ስህተት ነው። ከሥላሴ አካላት አንዱ የተቀሩትን እንዲውጥ ማድረግ 'ሞናርኪያኒዝም' የሚባለው አርዮሳዊ መሳይ ሐሳዊ ትምህርት ነው። በ1870ዎቹ የተጀመረው የይሆዋ ምስክሮች ትምህርትና በ1920ዎቹ የተጀመረው 'ኢየሱስ ብቻ' የሚባሉት የስህተት ትምህርቶች በባህርያቸው የዚህ ስህተት ቅርንጫፎች ናቸው። የመጀመሪያዎቹ አብን ብቻ አምላክ ያደርጋሉ። ሁለተኛዎቹ ደግሞ ወልድን ብቻ አምላክ ያደርጋሉ። ምናልባት መንፈስ ቅዱስን ብቻ እንደ አምላክ የሚቆጥሩ ሌሎች ደግሞ ይነሱ ይሆን?!

በሁለተኛውና በሦስተኛው ምዕተ ዓመታት ትልቅ ክርክር የተነሳበት የመለኮትን አሐዳዊ ሥሉስነት ለመግለጥ የተወሰደው ጊዜና ጉባዔ ጥቂት አልነበረም። የመንፈስ ቅዱስን ብቻ ሳይሆን የወልድንም አምላክነት የማይቀበሉ በአጠቃላይ የሥላሴን ኅልውና የሚክዱ ትምህርቶችና አዝማሚያዎች በዚህ ጊዜ ተከስተው ነበር። እነዚህ ትምህርቶች የእግዚአብሔርን አሐዳዊ ኅልውና እንደ ዘብ ሆነው በመጠበቅ በመለኮታዊ ኅልውና ውስጥ ሌላ አካል ከአምላካዊው ስልጣን መተካከል የለበትም የሚሉ ናቸው። ለነዚህ ትምህርቶች በአጠቃላይ የተሰጠው ስም "ሞናርኪያኒዝም" ወይም ብቸኛ ሉዓላዊነት የተሰኘ ሲሆን በአጠቃላይ ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች በዚህ ስህተት ውስጥ ይገኛሉ። እነዚህም "ዳይናሚክ ሞናርኪያኒዝም" እና "ሞዳሊስቲክ ሞናርኪያኒዝም" ናቸው። የመጀመሪያው ዓይነት ትምህርት ማለትም "ዳይናሚክ ሞናርኪያኒዝም" የተከሰተው በ190 ዓ.ም. ቴዎዶቶስ በተባለው ሰውና ከእርሱ በኋላም በተነሱት ተከታዮቹ ነው። የትምህርቱም አሳብ ወልድ ሲጠመቅ ነውና መንፈስ ቅዱስ የወረደበት እስኪጠመቅና ክርስቶስ ወይም የተቀባ እስኪሆን ድረስ አምላክ አልነበረም የሚል ነው። ይህ ትምህርት በ268 ዓ.ም.በተደረገው የአንጾኪያው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጉባዔ ስህተትነቱ ተነገረ። ሁለተኛው ዓይነት ስህተት ማለትም ሞዳሊስቲክ ሞናርኪያኒዝም የሚባለው ደግሞ፥ አንድ እግዚአብሔር ኖሮ ግን በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ አካላት ተገለጠ፤ ልዩነቱም

በተለያዩ ጊዜያት እንደአስፈላጊነቱ የተሰጠው የስም ልዩነት ብቻ እንጂ ሌላ አይደለም፤ ይህ አንዱ እግዚአብሔር አንዴ እንደ አብ፥ ሌላ ጊዜ እንደ ወልድ፥ ሌላ ጊዜ ደግሞ እንደ መንፈስ ቅዱስ ሆኖ ተገለጠ እንጂ በሦስት አካላት የተገለጠ አንድ አምላክ አይደለም የሚል ትምህርት ነው።

እነዚህ ትምህርቶች የመንፈስ ቅዱስን የሥላሴ አካልነት አይቀበሉም። ትምህርተ-ሥላሴን አይቀበሉትምና። እነዚህና ሌሎችም በዚህ ጊዜና በኋላም የተነሱት ስህተቶች መንፈስ ቅዱስን እንደ አንድ ኃይል ወይም ተጋቦት ብቻ ነው የሚመለከቱት። በ325 ዓ.ም. ከተደረገው የኒቅያ ጉባዔ በፊት ትልቅ ጥያቄ የነበረው በወልድ መለኮታዊ ኅልውና ላይ ነበር። በኒቅያው ጉባዔ በመንፈስ ቅዱስ የማመንንም ጥቅስ በመግለጫው አወጣ። ይሁን እንጂ ይህ ትምህርተ መለኮት በጥልቀት ያደገ አልነበረም። በኋላም በ381 በተደረገው የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት አበው የቁስጥንጥንያው ጉባዔ መንፈስ ቅዱስ "ከአብ የሚወጣው የሕይወት ጌታና ሰጪ፥ ከአብና ከወልድ ጋር የሚሰገድለት" በሚል ተገልጧል። ከቅዱስ አውጉስጢኖስ ትምህርት በኋላም ስለ መንፈስ ቅዱስ ስርዓት ከተከተለው ጥያቄ ቀጥሎ ከወልድም መሰረጹ ግልጽ የሆነበት "ፊሊዮክ" የሚለው ሐረግ በቶሊዶው ጉባዔ በ589 ዓ.ም. ተጨመረ። ይህ የሮማይስጥ ቃል ሲሆን "ከወልድም" ማለት ነው። የምሥራቁና የምዕራቧ ቤተ ክርስቲያን ቀድሞውንም የመለያየት ምልክቶች ቢታይባቸውም ይህም የራሱን አስተዋፅዖ አድርጎ ነበር። እንግዲህ እነዚህ ነጥቦች በቤተ ክርስቲያን ታሪክ የመጀመሪያዎቹ ምዕተ ዓመታት ውስጥ የታዩ የመንፈስ ቅዱስን መለኮትነት ለማስረዳት የተደረጉ እርምጃዎችና የተወሰዱ ውሳኔዎችን ያመለክታሉ። እነዚህ ጉባዔዎች ፍልስፍናዊ ሳይሆኑ መንፈሳዊና በቃሉ ላይም ተመስርተው የተደረጉ ነበሩ።

መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር የሚመለክና የሚሰገድለት አምላክ ነው። ከአምላክ ያነሰም አይደለም፥ የሥላሴን ኅልውና የሚውጥም አይደለም። መንፈስ ቅዱስ አምላክ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ አበክሮ ያስተምረናል። ዋና ዋናዎቹን እንመልከት።

መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ባህርያት አሉት። መለኮታዊ ባህርይ ማለት ከአምላክ ብቻ በቀር ማንም ፍጡር የሌለው ባህርይ ማለት ነው። ከነዚህ ባህርያት መካከል:-

ዘላለማዊ መሆኑ (ዕብ.9:14)

በሁሉ ቦታ መገኘቱ (መዝ.139:7-10)

ሁሉን ማወቁ (1ቆሮ.2:11)

ሙትን እንኳ ማስነሳት መቻሉ (ሮሜ.8:11) ናቸው።

የእርሱ ህልውና ጉዳይ ሲነሳ "መንፈስ ቅዱስ ምንድን ነው?" ሳይሆን "መንፈስ ቅዱስ ማን ነው?" ነው የምንለው። አካል ነው ስንል ሰውን ለመግለጥ የምንጠቀምባቸውን መግለጫዎች መንፈስ ቅዱስን ለመግለጥ እንጠቀማለን ማለት ነው። ይህ ማለት መንፈስ ቅዱስ ሰው ነው ማለት ፈጽሞ አይደለም። ነገር ግን ሰው የእግዚአብሔር አምሳል እንደመሆኑ መጠን መንፈስ ቅዱስ ደግሞ የሥላሴ አካል ማለትም እራሱ እግዚአብሔር እንደመሆኑ መጠን ይህ አምሳላዊ ግንኙነት የመንፈስ ቅዱስን አካልነት ይበልጥ ሊያስረዳን ይችላል። ሰው ሕያው አካል እንደመሆኑ መጠን የሚያደርጋቸውና የሚሆናቸው ወይም የሚሆኑበት ነገሮች የመንፈስ ቅዱስን ማንነት በተለይም አካልነት ሊያስረዱን ይችላሉ።

## መንፈስ ቅዱስ ሰብነት (አካል) ነው

መንፈስ ቅዱስ አካል መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያስተምረናል። አካል የመሆኑ ዋና ዋና ገላጮች ምን እንደሆኑ ቀጥሎ እንመለከታለን።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲናገር "እርሱ" በማለት የሚጠቀምባቸው የተባዕታዊ ፆታ ነጠላ ተውላጠ ስሞች አካልነቱን ያመለክታሉ። ሁሌም አብ ወይም ወልድ እርሱ እንደሚባሉ መንፈስ ቅዱስም እርሱ እየተባለ ይጠራል። (ዮሐ.14:16-17፤ ዮሐ.16:7-15)

- እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው...

- እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልከላችኋለሁ።

- እርሱም መጥቶ...ዓለምን ይወቅሳል።

- ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ...

እነኚህ ጥቂቶቹ ናቸው። መንፈስ ቅዱስ አካል ስለሆነ ሰዎች አካል የሆነን

ኀልው እንደሚያደርጉ ሊሰድቡት ሊቃወሙትም ይችላሉ (ዕብ.10:29፤ ሐዋ.7:51) በአማርኛችን የግዑዝ ፆታ መግለጫ ተውላጠ ስም የለንም። በሌሎች ቋንቋዎች (ለምሳሌ እንግሊዝኛ) ይህ መጥሪያ ቃል ሲኖረው አዲስ ኪዳን በተፃፈበት የግሪክ ቋንቋም የግዑዝ ፆታ መለያ ተውላጠ ስም አለ። ይሁን እንጂ መንፈስ ቅዱስ በተጠቀሰባቸው ቦታዎች ሁሉ በተባዕታዊ ፆታ ነጠላ ነው የተጠቀሰው።

- መንፈስ ቅዱስ ይፈቅዳል ወይም ፈቃድ አለው፥ ፈቃድ ማለት ደመ-ነፍስ ከምንለው ነገር የተለየ ነው። ሰውን ከእንስሳት ወይም ከአራዊት ከሚለዩት ጠባዮች አንዱ ይህ ፈቃድ የሚባለው ነገር ነው። መንፈስ ቅዱስ የወደደውን ለማድረግ ያልወደደውን ደግሞ ላለማድረግ የራሱ የሆነ ፈቃድ አለው። በ1ቆሮ.12:11 መንፈስ ቅዱስ እንደፈቀደ ስጦታዎችን እንደሚያካፍል ተጽፏል። በ2ጴጥ.1:21 ደግሞ ትንቢት በሰው ፈቃድ እንዳልመጣ ይልና መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ነድቶ እንዳስጻፋቸው ይናገራል። ከዚህም ቅዱስ ቃሉ በሰው ፈቃድ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ እንደተጻፈ እናስተውላለን።

- መንፈስ ቅዱስ ያስባል ወይም ያውቃል፥ ዕውቀት ማለት በአዕምሮ ተመራምረው የሚደርሱበትና የሚረዱት ነገር ነው። ሮሜ.8:26-27 መንፈስ ቅዱስ ልብን የሚመረምረው የመንፈስ አሳብ ምን መሆኑን ከማወቁ የተነሳ ስለ ቅዱሳን እንደሚማልድ ያስተምረናል። የልብን አሳብ ሳይቀር ያውቃል ማለት ነው። 1ቆሮ.2:11 ደግሞ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር የሆነውን ሁሉ እንደሚያውቅ ይነግረናል። እኛ አሳቢና አዋቂ ፍጡራን የሆንነው የእግዚአብሔር አምሳል ከመሆናችን የተነሳ ከአዋቂነቱም ከመካፈላችን የተነሳ ነው።

-መንፈስ ቅዱስ ስሜት አለው፥ ሰዎች ስለሆንን አንዳንድ ጊዜ እናዝናለን ሌላ ጊዜ እንደሰታለን ሌላ ጊዜ በቁጣ እንበሳጫለን እነዚህንና ሌሎች ስሜቶቻችንንም ወይ አፍነን እናቆያቸዋለን ወይም እናወጣቸዋለን እነዚህ ስሜቶቻችን ናቸው። ሰው ስሜት ያለው ፍጡር ነውና ይህ ምን ማለት መሆኑን አናጣውም። መንፈስ ቅዱስ ስሜት እንዳለው ከቃሉ እናገኛለን። ለምሳሌ በገላ.5:17 መንፈስ ቅዱስ እንደሚመኝና ይህም ምኞት ስጋ በመንፈስ ላይ ሊያሸንፍ እንደሚመኝ መንፈስም በሰው ውስጥ ባለ በስጋ ኃይል ላይ የበላይ ሊሆን የሚፈልግ ምኞት እንደሆነ እናነባለን። ያዕ.4:5ም ተመሳሳይ እውነት ይነግረናል። እንዲያውም በዚህ ክፍል መንፈስ ቅዱስ በቅንአት እንደሚመኝ እናያለን። ሌላ ሳይሆን የቅድስና ቅንዓት። ኤፌ.4:30 ለቤዛ ቀን የታተምንበትን እርሱን መንፈስ ቅዱስን እንዳናሳዝን ያስጠነቅቀናል። መንፈስ ቅዱስ ያዝናል

ማለት ነው።

መንፈስ ቅዱስ አካል ከሆነ አካላዊ ለሆነ ጎልውና እንደምንጠነቀቅና ጎልው በሆነ ፊት ራሳችንንም በብዙ መንገድ እንደምናዘጋጅ ሁሉ ከእርሱም ጋር ለሚኖረን ግንኙነት ጠንቃቃዎች ልንሆን ይገባናል። እርሱ ፈቃድ አለውና ልናስፈቅደው፥ ያውቃልና ልንጠይቀው፥ ያዝናልና ልንጠነቀቅለት ወዘተ. ያሻናል።

## መንፈስ ቅዱስ የሚመሰልባቸው ምሳሌዎች፤

መጽሐፍ ቅዱስ ለመረዳት የሚያስቸግሩ አሳቦችን ምሳሌያዊ በሆነ መንገድ ይፈታቸዋል። አንዳንዴ 'እንደ' የሚል ማመሳሰያ በመጠቀም ተመሳሳይነታቸውን ሲገልጥ አንዳንዴ ደግሞ ሁለት የተለያዩ ነገሮችን ቀጥታዊ በሆነ መግለጫ አመሳስሎ ያስረዳል። ለምሳሌ ጌታ ራሱን በወይን ግንድ ሲመስል የወይን ተክል መሆኑን መናገሩ ሳይሆን የግንኙነት መግለጫ አድርጎ መጠቀሙ ነው። አንዳንድ ክርስቲያኖች መንፈስ ቅዱስ ወደ ሕይወታቸው ሲገባ ከነዚህ ምልክቶች መካከል አንዱ ወይም ጥቂቱ አካላዊ በሆነ መንገድ እንዲታያቸው ይከጅላሉ። ለምሳሌ በዘይት ሲቀቡ ውኃ ሲፈስባቸው ወይም እሳት ሲወርድባቸው ሊያዩ በጣም ይጓጓሉ። መጥፎ ጉጉት አይደለም ግን ትክክለኛ አጠባበቅም አይደለም።

እግዚአብሔር ማንነቱ በተምሳሌታዊ መግለጫዎች ሲገለጥ ዓለት፥ ጋሻ፥ ብርሃን ወዘተ. ተብሏል። ጌታም በግ፥ በር፥ መንገድ፥ ወዘተ. ተብሏል። መንፈስ ቅዱስም ከታች በተዘረዘሩት ምስሎች ሲገለጥ የአገላለጡን ዓላማ ዘንግተን ርግብ ባየን ቁጥር ወይም አውሎ ነፋስ የተሰበሰብንበትን ቤት ጣራ ቢገነጥል መንፈስ ቅዱስ የመጣ እስኪመስለን ድረስ መሳሳት የለብንም።

መንፈስ ቅዱስ የሚመሰልባቸው ሰምንት ያህል ተምሳሌቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተገልጠዋል። እነዚህም ውኃ፥ ዘይት፥ ርግብ፥ እሳት፥ ነፋስ፥ መያዣ፥ ልብስና ማህተም ናቸው። መንፈስ ቅዱስ ርግብ ወይም ዘይት ነው ማለት አይደለም። ነገር ግን እነዚህ ስያሜዎች ባሕርያቱን ለመግለጥ ቃሉ የተጠቀመባቸው ምሳሌዎች ወይም ምስሎች ናቸው።

## ሀ) ርግብ

ርግብ የየውሃት፣ የንጽህና፣ የእረፍትና የሰላም ምልክት ናት። ጌታ በመጥምቁ ዮሐንስ እጅ በተጠመቀ ዕለት አብ ከሰማያት በመናገር፣ ወልድ በመጠመቅ፣ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በወልድ ላይ በመውረድና በማረፍ የሥላሴ ኅልውና ተገልጦ ነበር። በዚህ ቀን የሆነውን የመንፈስ ቅዱስ መውረድ አራቱም ወንጌላት አስፍረውታል።

- ማቴ.3:16 "የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ።"

- ማር.1:10 "መንፈስም እንደ ርግብ ሲወርድበት አየና..."

- ሉቃ.3:22 "መንፈስ ቅዱስም በአካል መልክ እንደ ርግብ በእርሱ ላይ ወረደ።"

- ዮሐ.1:32 "መንፈስ ቅዱስ ከሰማይ እንደ ርግብ ሆኖ ሲወርድበት አየሁ በእርሱ ላይም ኖረ።"

መንፈስ ቅዱስ እንደ ርግብ ሆኖ መውረዱ ነው የነዚህ ጥቅሶች ዋና አሳብ። መንፈስ ቅዱስ ርግብ ሆኖ አልወረደም ወይም ራሱ በርግብ ተመስሎ አልወረደም። ከጥቅሱ እንደምንረዳው እርሱ ሳይሆን አወራረዱ ነው እንደ ርግብ የተመሰለው። እሳትን ወይም ነፋስን የወሰድን እንደሆነ ኃይልን ያመለክታሉ። የርግብ አወራረድ ግን ሰላማዊ የሆነ ስመመንን እንደሚያመጣ ያለ፣ ጸጥታን የተሞላ፣ ደስታን የሚፈጥር ዓይነት ነው። በልምድ እንደምናውቀው መንፈስ ቅዱስን ለመግለጥ የርግብ ስዕል ይሳላል፤ ይህ ስዕል ተምሳሌታዊ እንጂ በአካል መንፈስ ቅዱስ ርግብ የመሆኑ ማረጋገጫ አይደለም።

ከነዚህ ጥቅሶች ሁለት ዋና ዋና አሳቦችን በማስተዋል እንወስዳለን። እነዚህም መውረድና መኖር ናቸው። በመጀመሪያዎቹ ሦስት ጥቅሶች ሲወርድ ስናይ በዮሐንስ ወንጌል ግን ሲወርድና ሲኖር እናነብባለን። ርግብ ድንጉጥና የዚያኑ ያህል ደግሞ ታማኝ ወፍ ናት። አንዴ ከተያዘችና ወደ ጎጆዋ ከገባች በኋላ የምታርፍ ለማዳ ነገር ናት። መንፈስ ቅዱስም ወደ አማኝ ሲገባ ገብቶ ሊወጣ ሳይሆን ገብቶ ሊኖር ነው የሚመጣው።

## ለ) ውኃ

በዮሐ.7:37-39 ላይ "ከበዓሉም በታላቁ በኋላኛው ቀን ኢየሱስ ቆሞ ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ። በእኔ የሚያምን መጽሐፍ

እንዳለ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል ብሎ ጮኸ። ይህን ግን በእርሱ የሚያምኑ ሊቀበሉት ስላላቸው ስለ መንፈስ ተናገረ ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ገና አልወረደም ነበርና" የሚል ቃል ተጽፏል። ይህ በዓል የዳስ በዓል ሲሆን የመጨረሻው ቀን የበዓሉ ማሳረጊያ ትልቁ ቀን ነው። የዳስ በዓል እስራኤል በምድረ በዳ የሄዱበትና በድንኳን የኖሩበት ዘመን ማስታወሻ በዓል ነው። በዚህ የ40 ዓመታት የደረቅ መሬት ጉዟቸው እግዚአብሔር ለምግባቸው መናን ከሰማይ እያወረደ ለእርካታቸው ደግሞ ከዓለት ውኃን አመንጭቶ አጠጥቷቸዋል። በልማዳቸው መሠረት በዚህ ቀን ሊቀ ካህናቱ በእንስራ ውኃ ይዞ የሚናፍቁትን እርካታና ምስጋና የሚገልጽ ቃል ተናግሮ ውኃውን የደረቀው መሬት ላይ ያፈስሰዋል። በዚህ በዓል ሊቀ ካህናቱ ውኃውን እመሬት ላይ የሚያፈስሰው ለምድረ በዳው የጌታ ሥራ ማስታወሻ ሲል ነው። ጌታ ይህንን ጥሪ ልክ በዚህች ጊዜ ማቅረቡ የእርካታው ምንጭ እርሱ መሆኑን ይገልጻል። ይህ ክፍል ስለ እምነት ስለሚናገር ስለ ደኅንነት መናገሩ ግልጽ ነው። የእርካታው ምንጭ አማካይ የሆነው መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ውስጥ መኖር የሚጀምረውና በዚያም ሰው የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ የሚፈልቀው ያ ሰው በጌታ ሲያምን ነው። መንፈስ ቅዱስ እዚህ ስፍራ በውኃ መመሰሉ እርካታን ሰጪ ብቻ ሳይሆን እንዲያውም የሚያረካን ነገር አመንጪ በመሆኑ ነው።

### ሐ) ነፋስ

መንፈስ የሚለው ቃል በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን ቋንቋ ነፋስ ከሚለው ቃል ወይም አሳብ ጋር ይቀራረባል ይመሳሰላልም። ጌታ ለኒቆዲሞስ ዳግመኛ ስለመወለድና ይህም ልደት ከመንፈስ ስለመሆኑ ከነገረው በኋላ በዮሐ.3:8 "ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል ድምፁንም ትሰማለህ ነገር ግን ከወዴት እንደመጣ ወዴትም እንዲሄድ አታውቅም ከመንፈስ የተወለደ ሁሉ እንዲሁ ነው" አለው። በሐዋ.2:2 በጴንጤቆስጤቀን ስለሆነው ነገር ሉቃስ ሲጽፍ "ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምጽ መጣ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው" ይላል።

በነዚህ ጥቅሶች ከነፋስ ባህርያት ጥቂቶቹን እናገኛለን። እነዚህም አለመታየትና ኃይል ናቸው። ነፋስ አይታይም ከየትም ተነስቶ ወዴት እንደሚሄድ መናገር አንችልም። ፊታችንን ሲያቀዘቅዝ፥ ዛፎችን ሲያወዛውዝ፥ ሌሎችንም ነገሮች ሲያደርግ ስራውን ግን እናያለን። ነፋስ የሚነጥቅ፥ የሚያፈርስ፥ የሚነቅል፥ ሌሎችንም ነገሮች የሚያደርግ ኃይል አለው። የመንፈስ ቅዱስ ስራው በነፋስ አሰራር ይመሰላል። መንፈስ ቅዱስ ኃይል ያለው አምላክ እንጂ እርሱ ራሱ 'ኃይል ብቻ' አለመሆኑ መጤን አለበት።

## መ) እሳት

በማቴ.3:11-12 መጥምቁ ዮሐንስ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት የሚያጠምቅ መሆኑን ተናገረ። በሐዋ.2:2 መንፈስ ቅዱስ በወረደ ዕለት በዚያ ተሰብስበው ለነበሩት እንደ እሳት ወይም ነበልባል የተከፋፈሉ ልሳኖች እንደታዩአቸውና በላያቸውም እንደተቀመጡባቸው ተጽፏል። እሳት በብሉይ ኪዳንም የእግዚአብሔር ኀልውናና መገኘት ተምሳሌት በመሆን ይታይ ነበር። ለምሳሌ ለሙሴ እግዚአብሔር በቁጥቋጦው ተገልጦ በተናገረው ጊዜ ሙሴ ያየው የእሳት ራዕይ ነበር። በምድረ በዳ ጉዞአቸው ዘመናት የምሪቱም የጥበቃውም ምልክት ይሆን ዘንድ በእሳት ዓምድ ይመራቸው ነበር። (ዘጸ.3:2፤ ዘጸ.13:21) እሳት የማያስፈልግ ገለባን የሚበላና የሚያጠፋ እንዲሁም የእግዚአብሔርንም ቁጣና ፈራጅነት የሚያመለክት ነው። (ዕብ.12:29) እሳት የሚያጠራ ማንጠሪያና የሚያነጻ ነገርም ነው። ክርስቲያን ሊቀደስ የሚችለው ቅዱሱ መንፈስ በእርሱ ውስጥ ሊያድር ሲጀምር ብቻ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ስራ እሳታዊ ሥራም ነው። ይህ ሲባል መንፈስ ቅዱስ ወደ ክርስቲያን ውስጥ ሲገባ አካላዊ እሳት ሆኖ ይገባል ማለት አይደለም። ነገር ግን የሙቀትን፥ የግለትን፥ ገለባን የማጥራትን፥ ብርሃን የመሆንንና የመሳሰሉትን ስራዎች በአማኞች ውስጥ የመስራቱ ምልክት ነው።

## ሠ) ልብስ/ኃይል

በሉቃ.24:49 ጌታ ሐዋርያቱን "እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ" አላቸው። ልብስ አንዳንድ ጊዜ የዕርቃን መሸፈኛ ብቻ ሳይሆን መለያ ነው ጌጥም ይሆናል የኃይልም ምልክት ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው ተራ የቤት ልብሱን ለብሶ መስቀለኛ መንገድ ላይ ቆሞ መንገደኞችንና ተሽከርካሪዎችን ሊያጋፍር ቢሞክር መታዘዝን ያለማትረፍ ብቻ ሳይሆን ምናልባት ሕይወቱንም ሊያጣ ይችላል። ያው ሰው ግን የትራፊክ ደንብ ለብሶ (ወይም ሆኖ) ቢቆም ከልብሱ ጋር ኃይል አለና መልካም ተግባርን ሊያከናውን ይችላል። ያ የትራፊክ ፖሊስ ልብስ ብቻ ሳይሆን ኃይልና ሥልጣንም ነው የለበሰው። ጌታ የተናገራቸው ልብስ ለምስክርንት ለአገልግሎት የሚታጠቁትን ኃይልና ሥልጣን የሚያመለክት ነው። ለመልበስ እንዲጠብቁ የተነገራቸው ከበዓለ ኀምሳ በፊት የነበሩት አማኞች ነበሩና ከበዓለ ኀምሳ ወዲህ ይህን ኃይል ለመልበስ ልዩ ጥበቃ አላስፈለገም።

ረ) ዘይት

ዘይት ለቅባትነት የሚውል፥ ለእይታ የሚስብ፥ ሞገስ ያለው ወፍራም ፈሳሽ ነው። እንደ መድኃኒትም እንደ ማለስለሻና ማለዘቢያም እንደ ምግብም እንደ መስዋዕትም ቅባት እንደ ብርሃን ምንጭም እንደ መውዣና እንደ ጌጥም ያገለግላል። ከነዚህም ሁሉ በተጨማሪ ደግሞ እንደ ስልጣን መቀበያ ምልክትም ሆኖ ያገለግላል (ለምሳሌ ነገስታት 1ሳሙ.10:1፤ 2ነገ.9:3 ካህናት ዘሌዋ.8:30 ነቢያት 1ነገ.19:6፤ ኢሳ.61:1) ይህ መቀባት ምልክታዊ ሆኖ ከእግዚአብሔር ስልጣንን የመቀበላቸው ወይም በእርሱ የመሾማቸው ምሳሌ ነው። በአዲስ ኪዳን ክርስቶስ የተቀባ ሆኖ እናገኘዋለን። ክርስቶስ ማለት እራሱ የቃሉም ትርጉም 'የተቀባ' ማለት ነው። (ሉቃ.4:18 እና ሐዋ.10:38) በግሪክ ቋንቋ 'ክሪዝማ' ማለት ቅባት ማለት ሲሆን 'ክርስቶስ' ማለት ደግሞ የተቀባ፥ ቅቡዕ ማለት ነው። ከዚህም በተጨማሪ የተወሰኑ ወይም የተለዩ ጥቂቶች ብቻ ሳይሆኑ አማኞች በሙሉ ደግሞ የተቀቡ መሆናቸውን እናነብባለን። (1ዮሐ.2:20) የተቀቡትም በመንፈስ ቅዱስ ነው። ከዚህ ቅባት ያልተቀበለ ወይም በመንፈስ ቅዱስ ያልተቀባ ማንም አማኝ የለም። አንድ ክርስቲያን ገና ክርስቲያን ሲሆን በዚህ ቅባት የተቀባ ነው። ይህ መቀባት በተለምዶ "እገሌ የተቀባ አገልጋይ ነው" እንደሚባለው አይደለም። ይህ አባባል ልማዳዊ እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም።

ሰ) መያዣ

ይህ ቃል በአጭሩ ቀብድ እንደማለት ነው። የንግድ ቋንቋ ሲሆን ዋናው ክፍያ ገና የሚቀር ሆኖ እንደ ዋስትና የሚሰጥ የመጀመሪያ ክፍያ መሆኑ ነው። ታማኝነትንና ወደ ፊት የሚደረግን የተሟላ ክንዋኔን የሚያመለክት የተስፋ ማስሪያ ነው። "አሁን ተጀምሯል ወደፊት ያልቃል" እንደማለት ነው። በአዲስ ኪዳን ትምህርት መንፈስ ቅዱስ ለአማኞች እንደተሰጠ መያዣ ተደርጎ ተስተምሯል። (ኤፌ.1:14፤ 2ቆሮ.1:22 እና 5: 5፤ 2ጢሞ.1:14) ይህ የሚያሳየን እግዚአብሔር በአማኝ ልጆቹ የጀመረውን የደኅንነት ዕቅድ አንድ ቀን በእርግጥ ወደ ፍፃሜ እንደሚያደርሰውና ይህን ሰውነታችንን በቤዛ ቀን ሙሉ በሙሉ እንደሚቤዠው ነው። አማኞች ሁሉ ይህን የመንፈስ መያዣ የተቀበሉት ጌታን በተቀበሉባት ቅጽበት ነው።

ሸ) ማኅተም

ማኅተም ማለት ስም ወይም ምስል የተቀረጸበት መታወቂያ የማረጋገጫ

ምልክት ነው። ማኅተም የታተመበት ነገር ስልጣንን፥ እውነተኛነትን፥ ባለቤትነትን፥ ጥበቃን ወይም መጠበቅን፥ የውል ፍጻሜንና ሌሎችም እንደ ጊዜና በታው የሚለያዩ ተግባሮችን ርግጠኝነትና ጥብቅነትን ያመለክታል። (አስ.8:8-10፤ ኤር.32:10፤ ዳን.6:16፥ 9:24 ፤ ማቴ.27:66፤ ራዕይ 5:1) በብሉይ ኪዳን ግዝረት አይሁድ የእግዚአብሔር የመሆናቸው ማኅተም ወይም ምልክት ነበር። (ዘፍ.38:18 እና 25) አዲስ ኪዳን በመንፈስ እንደታተምን ሲናገር ከላይ የተጠቀሱትን እውነቶች ማንጸባረቁ ነው። (ኤፌ.1:13 እና 4:30 ፤ 2ቆሮ.1:22) አማኞች ሁሉም ጌታን በተቀበሉ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ የታተሙ ናቸው።

እንግዲህ እኚህ ከላይ የተመለከትናቸው ምሳሌዎች ሁሉ ምሳሌዎች ብቻ በመሆናቸው ያለቅጥ ተለጥጠው ስህተት ውስጥ እስኪከትቱ ድረስ ነገሮቹ እንደ መንፈስ ቅዱስ ወይም መንፈስ ቅዱስ እንደነገሮቹ ተደርገው መወሰድ የለባቸውም። እነዚህ ነገሮች ውሱን ለሆነው አዕምሯችን የመንፈስ ቅዱስን ማንነትና ስራውንም እንድናገናዝብ የተሰጡን ምሳሌዎች ብቻ እንደሆኑ መዘንጋት የለብንም።

## የመንፈስ ቅዱስ ተግባራት በብሉይ ኪዳን

### ሀ. የፍጥረት ሥራ

መንፈስ ቅዱስ ፈጣሪ አምላክ ነው። ስለዚህም ዓለማትም ሆኑ ሰው ሲፈጠር በሥላሴ የፍጥረት ሥራ ተካፋይ ነበር። በዘፍ.1:2 እና መዝ.33:6 እንደምናገኘው ሰማያት የተፈጠሩትና የጸኑትም በመንፈስ ቅዱስ ነው። በኢዮ.33:4 ደግሞ "የእግዚአብሔር መንፈስ ፈጠረኝ ሁሉንም የሚችል የአምላክ እስትንፋስ ሕይወትን ሰጠኝ" ይላል።

### ለ. ለሰዎችና ለመሪዎችም ስጦታን፥ ጥበብን፥ ኃይልንም መስጠት

ቤተ መቅደሱ በሚሰራበት ጊዜ በቤተ መቅደሱ ውስጥና ውጪ የሚገኙትን ዕቃዎች እንዲሁም የካህናቱን ልብሶችና ሌሎችም ነገሮች እንዲሰሩ ጥበብን እግዚአብሔር ሰጣቸው። (ዘጸ.31:1-11) በተለይ በቁጥር 3 ላይ

ባስልኤል ስለተባለው ሰው እንዲህ ተብሎ ተጽፏል። "በሥራ ሁሉ ብልሃት፥ በጥበብም፥ በማስተዋልም፥ በዕውቀትም የእግዚአብሔርን መንፈስ ሞላሁበት።" የእስራኤልንም መሳፍንትንና መሪዎች በላያቸው በመውረድ በልዩ ኃይል እያስታጠቀ ያሰማራቸው ነበር። ለምሳሌ በሙሴ (ዘኁ.11:17) በኢያሱ (ዘኁ.27:18) በጎቶንያል (መሳ.3:10) በጌዴዎን (መሳ.6:34) በዮፍታሔ (መሳ.11:29) በሶምሶን (መሳ.14:6 እና 19 እንዲሁም 15:14-15) በሳኦል (1ሳሙ.10:10 እና 11:6) በዳዊት (1ሳሙ.16:13)።

## ሐ. ለነቢያትና ለሌሎችም አገልጋዮች እንዲሁም ለብሉይ ኪዳን ጸሐፊዎች ጥበብንና ማስተዋልን መስጠት።

ነቢያት የእግዚአብሔርን መልእክት የሚናገሩ የብሉይ ኪዳን መልእክተኞች ናቸውና መልእክታቸው ፍጹምና ትክክለኛ ይሆን ዘንድ መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ በማደር ይሰራ ነበር። በዮሴፍ ኖሮ ሰርቷል። (ዘፍ.41:38) ምንም እንኳ እነርሱ ቢያሳዝኑትም እስራኤልን ይመራ ነበር። (ነህ.9:20፤ ኢሳ.63:10) ዳዊት ሲናገር "የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ተናገረ ቃሉም በአንደበቴ ላይ ነበረ" አለ። (2ሳሙ.23:2) በሌሎቹም ነቢያት መንፈስ ቅዱስ ሲሰራ እናያለን። ለምሳሌ በእስራኤል ሽማግሌዎች (ዘኁ.11:25) በሕዝቅኤል (ሕዝ.2:2) በሚክያስ (ሚክ.3:8) በዓዛርያስ (2ዜና.15:1) በካህኑ ዘካርያስ። (2ዜና.24:20)

# የመንፈስ ቅዱስ ተግባራት በአዲስ ኪዳን

መንፈስ ቅዱስ እንደ ብሉይ ኪዳን ጊዜ ሁሉ በአዲስ ኪዳንም ሳያቋርጥ ይሰራ ነበር። እንዲያውም ከብሉይም ኪዳን ይልቅ ልቀት ያለው ስራ ነው በአዲስ ኪዳን የሰራው።

## ሀ. ክርስቶስን በተመለከተ

የጌታን ሕይወት ከልደቱ እስከ ትንሳኤው ድረስ ስንመረምር በመንፈስ ቅዱስ የተደገፈ ሆኖ እናገኘዋለን።

የጌታን ሕይወት ከልደቱ እስከ ትንሳኤው ድረስ ስንመረምር በመንፈስ ቅዱስ የተደገፈ ሆኖ እናገኘዋለን።

- በመንፈስ ቅዱስ ተጸነሰ (ሉቃ.1:35፤ ማቴ.1:18-20)
- በመንፈስ ቅዱስ ተመራ (ማቴ.4:1)
- በመንፈስ ተሞላ (ሉቃ.4:1)
- በመንፈስ ቅዱስ ተቀባ (ሉቃ.4:18፤ ሐዋ.10:38)
- በመንፈስ አገለገለ (ማቴ.12:28)
- በመንፈስ ሐሴት አደረገ (ሉቃ.10:21)
- ሲሞትም ራሱን ለእግዚአብሔር ያቀረበው በዘላለም መንፈስ አማካይነት ነው (ዕብ.9:14)
- ከሞትም የተነሳው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ነው (ሮሜ.1:4 እና 8:11 እንዲሁም 1ጴጥ.3:18)
- ከትንሳኤውም በኋላ ሐዋርያቱን ያዘዛቸው በመንፈስ ቅዱስ ነው፤ (ሐዋ.1:2)

## ለ. ዓለምን ወይም ያልዳኑ ሰዎችን በተመለከተ

ዓለምን ይወቅሳል (ዮሐ.16:7-11) ይህ ወቀሳ ስለ ኃጢአት፥ ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድ ነው። ይህን የሚያደርገውም በዳኑት አማካይነት እነርሱን በመድረስ ነው እንጂ ባላመኑት ውስጥ በማደር አይደለም።

## ሐ. ቤተ ክርስቲያንን በተመለከተ

ቤተ ክርስቲያን ማለት የአማኞች ጉባዔ ወይም ኅብረት ማለት ሲሆን ይህ ጉባዔ የተመሰረተው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ማለትም መንፈስ ቅዱስ በኖረባቸው ሰዎች ኅብረትና አገልግሎት ነው። ይህ ኩላዊዋን ወይም ሁሉ-አቀፏን ቤተ ክርስቲያን በተመለከተ ነው። ያለ መንፈስ ቅዱስ ህልውና ቤተ ክርስቲያን አትኖርም (ኤፌ.2:19-22) ከዚህም ሌላ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥም መንፈስ ቅዱስ የሚሰራው ስራ አለው።

- አገልጋዮችን መሾምና ማሰማራት (ሐዋ.13:2-4 እና 16:6-10)
- የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን መሾም (ሐዋ.20:28)
- በመሪዎች ውሳኔ መግባት (ሐዋ.15:28)
- አማኞችን መናገርና ማስጠንቀቅ (1ጢሞ.4:1፤ ራዕ.2:7)

## መ. የበዓለ ኀምሳን ዕለት በተመለከተ

መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን ዘመንም ይሰራ እንጂ በአዲስ ኪዳን ልቀቱ ልዩ በሆነ መንገድ መስራት የጀመረው ከበዓለ ኀምሳ ዕለት ጀምሮ ነው። እንደ ኤች.ኤል.ዊልሚንግተን አገላለጽ ይህ ልቀት በሦስት መንገዶች ነው የተፈጸመው። አንደኛው ሁሉን አቀፍ ባህርይው ነው፤ አስቀድሞ ለአንድ ወገን ማለትም ለእስራኤል ብቻ የነበረው አሁን ሁሉን አቀፍ ሆነ። ሁለተኛው በአማኞች ለዘለቄታው ሊኖር መምጣቱ ነው። በብሉይ ኪዳን ከአንዳንድ ሰዎች ምሳሌ እንደምንረዳው መንፈስ ቅዱስ በሰዎች ውስጥ በዘላቂነት አልኖረም። ለምሳሌ ሶምሶን (መሳ.14:6 እና 16:20) ሳኦል (1ሳሙ.10:10 እና 16:14) ዳዊትም በመዝ.51:11 ካቀረበው ልመና ይህን እንረዳለን። ሦስተኛው ደግሞ ፍጹም የማድረግ ስራው ነው።

ይህ ማለት አዲሱ አገልግሎቱ አሁን ንስሃ የሚገቡ አማኞችን በሙሉ በጸጋው እንዲያድጉና ክርስቶስን እንዲመስሉ ማድረግ ነው። በብሉይ ኪዳን እንዲህ አልነበረም። የሳኦልም ሆነ የሶምሶን ግብረ-ገባዊና መንፈሳዊ ባህርያቸው በመንፈስ ቅዱስ በእነርሱ መኖር እንደተሻሻለ ምንም አመልካች ውጤት አናገኝም። እንደሚመስለው እነዚህ ከእርሱ የተቀበሉት ኃይሉን ብቻ እንጂ ቅድስናውን አልነበረም።[3]

ይህ የበዓለ ኀምሳ ቀን መንፈስ ቅዱስ ይፋዊ በሆነ መንገድ የወረደበት ዕለት ነውና የሚደጋገም አይደለም። የአዳኛችን የክርስቶስ ልደት በበረት ውስጥ አንድ ጊዜ እንደተፈጸመ አንድ በዓለ ኀምሳ ብቻ ነው ሊኖረን የሚችለው፣ ያለውም።

## ሠ. ነፍስ ወከፍ (እያንዳንዱ) አማኝን በተመለከተ

አንድ ሰው ከመዳኑ በፊት በመንፈስ ቅዱስ እንደሚወቀስ ተመልክተናል። ክርስቶስን በማወቅና በመቀበል ወደ ደኅንነት ሲመጣና ከመጣ በኋላ መንፈስ ቅዱስ በዚያ ሰው ውስጥ አስደናቂ ስራዎችን መስራት ይጀምራል ይቀጥላልም። መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ሕይወት ውስጥ አምስት ግልጥ የሆኑ ሥራዎችን ይሰራል። እነዚህም፤

1. ዳግም እንዲወለድ ያደርጋል (ዮሐ.3:3-7 እና ቲቶ. 3:5)

2. አማኙ በዚያኑ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ይጠመቃል፤ ሮሜ.6:3-4፤ 1ቆሮ.12:13፤ ገላ.3:27፤ ቆላ.2:12)

3. በመንፈስ ቅዱስ ይታተማል (2ቆሮ.1:22፤ ኤፌ.1:13 እና 4:30)

4. መንፈስ ቅዱስ ከዚህ ዕለት ጀምሮ በአማኙ ውስጥ መኖር ይጀምራል (ዮሐ.14:16፤ ሮሜ.8:9፤ 1ቆሮ.3:16፤ 1ዮሐ.3:24) ከዚህ በኋላ አማኙ የሚኖረው ኑሮ የተለወጠ ኑሮ ነው። መመላለሱም በመንፈስ መመላለስ ይባላል። (ገላ.5:16-18)

5. አማኙን ይሞላዋል (ሐዋ.2:4፤ ሐዋ.4:8፤ ሐዋ.6:3፤ ሐዋ.7:55፤ ሐዋ.9:17፤ ሐዋ.11:24፤ ሐዋ.13:9 እና 52፤ ኤፌ.5:18) ይህ ሙላት የአንድ ጊዜ ክስተት ብቻ ሳይሆን የሚቀጥልና መቋረጥ የሌለበት የመንፈስ ቅዱስ ስራ ነው።

መንፈስ ቅዱስ በአንድ አማኝ ውስጥ በሚኖርበት ጊዜ አሳቡንና ፈቃዱን በዚያ አማኝ አድርጎ ሊፈጽም ይችላል። ለምሳሌ ወደ እውነት መምራት (ዮሐ.16:13)፣ የእግዚአብሔርን ፍቅር በዚያ ሰው ልብ ውስጥ ማፍሰስ (ሮሜ.5:5)፣ ለአገልግሎት ኃይልን ማስታጠቅ (ሐዋ.1:8)፣ ከዚህም ሌላ መንፈስ ቅዱስ የራሱንም ባህርይ በዚያ ሰው ውስጥ ሊያንጸባርቅ ይችላል ለምሳሌ ይቀድሰዋል (1ተሰ.5:23) የመንፈስ ፍሬን በውስጡ ያፈራል፣ (ገላ.5:22) ደግሞም ክርስቶስን እንዲመስል ይቀርጸዋል። (2ቆሮ.3:18) እኛም በዚህ ዘመን የምንኖር አማኞች በአዲሱ ኪዳን ውስጥ የምንኖር አማኞች

በመሆናችን ጌታን ከተቀበልንባት ቅጽበት አንስቶ መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ ይኖራል። እኛ ደግሞ ራሳችንን ሳንቆጥብና ሳናሰልስ ለእርሱ ብንሰጠው የእርሱ ግሩም ባህርይ እና ድንቅ አሰራር በሕይወታችን ይገለጣል። ከጊዜ ወደ ጊዜም ክርስቶስን እየመሰልን በእርሱ እናድጋለን።

መንፈስ ቅዱስ ሀይሉውናውን በክርስቲያን ውስጥ የሚገልጥባቸው ሁለት ትላልቅ መንገዶች አሉ። እነርሱም የጸጋ ስጦታዎችና የመንፈስ ፍሬዎች ናቸው። ፍሬው በሕይወታችን የሚታይ ስጦታው ደግሞ በአገልግሎታችን የሚገለጥ ነው። እኒህ ሁለት ነገሮች አንዱ ከሌላው የሚጋጩ ወይም የማይገናኙ ሳይሆኑ አንዱ ሌላውን የሚያውቡና የሚያቆነጁ እርስ በርሳቸውም የሚደጋገፉ ናቸው። ፍሬ ማፍራት መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ውስጥ በመሆን ሲቆጣጠረው ከሚያደርጋቸው ስራዎች አንዱ ነው። እግዚአብሔር እኛን ልጆቹን ፍሬያማ ልጆች ልንሆንለት ይሻል። ቃሉም ይህን ይመከረናል፥ ያዘናልም። (መዝ.1:3፤ ዮሐ.4:35-36 እና 15:1-16፤ ሮሜ 6:22 እና 7: 4፤ ገላ.5:22-23፤ ቆላ.1:10) እነዚህ ፍሬዎች፥

- ከውጪ የሚታዩ ነፍሳትን የመማረክና የማብዛት ነገር ያለባቸው፥
- በክርስትና ሕይወት የመመላለስ ውበት የሚንጸባረቅባቸው፥ እና
- በአማኙ ሕይወት ውስጥ የክርስቶስን መልክ የሚስሉ ናቸው። በተለይ በገላ.5:22-23 ውስጥ የተዘረዘረውን ፍሬ ብናይ ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግስት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የዋህነት እና ራስን መግዛት ተብሎ ተጽፏል። ይህ ዝርዝር በውስጡ እነዚህን ዘጠኝ ነገሮች ቢይዝም 'ፍሬዎች' ሳይሆን 'ፍሬ' ነው የተባለው። ብዙዎች ፍሬዎች ሳይሆኑ ሁሉንም የያዘ አንድ ፍሬ ነው። በአንድ ዘለላ እንዳሉ ብዙ የወይን ፍሬዎች ሳይሆን ልክ በአንዱ ፍሬ ውስጥ ብዙ ትናንሽ ፍሬዎች እንዳሉበት ሮማን መሳይ ነገር ነው። ስለዚህ የመንፈስ ፍሬ ነገር ከተነሳ አንድ አማኝ "ፍቅር አለኝ ደስታ ግን የለኝም" ወይም "በጎነትን እችላለሁ ራሴን መግዛት ግን ያቅተኛል" ማለት አይችልም፡ አይገባውምም። የጸጋ ስጦታ ነው አንዱ ኖሮ ሌላው ላይኖር የሚችለው እንጂ የመንፈስ ፍሬ ሁሉም መኖር አለበት። የመንፈስ ፍሬ አንድ ነው፤ በውስጡ ብዙ ፍሬዎች ያሉበት አንድ የመንፈስ ፍሬ። ያ አንድ ካለ ሁሉም አሉ። ከሌለ የለም ማለት ነው እንጂ ከፊል ኖሮ ከፊል የማይኖርበት ምንም መንገድ የለም።

የመንፈስ ፍሬ መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን እየገዛና እየሰለጠነ ማለትም ባለስልጣን እየሆነ ሲሄድ ቃሉን በማጥናትና በማሰላሰል ምሪቱን ስንከተል

ሌሎች ክርስቲያኖችም በኛ ውስጥ የሚያዩአቸውን ግድፈቶችና ኃጢአቶች ለማረም ሲያመለክቱን እኛም ያንን እሺ በማለት ስንታዘዝና ስንስተካከል የሚታይ ውጤት ነው። የመንፈስ ፍሬ በመንፈስ ቅዱስ እየተሞላ የሚኖር ክርስቲያን ባህርይ ነው። የእውነተኛና ታዛዥ ክርስቲያን ምልክትና መታወቂያ የመንፈስ ፍሬ እንጂ የጸጋ ስጦታ አይደለም። ይሁን እንጂ ማንኛውም ክርስቲያን የመንፈስ ፍሬ ስለመላው (ስለሚታይበት) ብቻ ለአገልግሎት ብቻ ብቁ ነው ማለት አይደለም። ለማገልገል የጸጋ ስጦታ ያሻዋል፥ የጸጋ ስጦታውንም ማወቅ፥ አውቆም በዚያው መሰማራት ይጠበቅበታል። በሚሰማራበት ጊዜ ግን በፍሬው ያልታጀበ አገልግሎት ቢያገለግል ከንቱና የማይጠቅም ነው። 1ቆሮ.13:1-3 የሚነግረን ይህን እውነት ነው። አንድ ሰው በልሳኖች ቢናገር ዕውቀትን ቢያውቅ እምነት ቢኖረውና ተራሮችን ቢያፈልስ ፍቅር ግን ከሌለው ከንቱ ነው። ፍቅር ደግሞ ስጦታ ሳይሆን ፍሬ ነው። ለዚህም ነው ጳውሎስ በ1ቆሮ.12 ላይ የስጦታዎችን ዝርዝርና አሰራር በ1ቆሮ.14 ደግሞ ሥነ-ሥርዓቱን ጽፎ በሁለቱ መካከል የመንፈስ ፍሬ ስለሆነው ስለ ፍቅር ያተተው። የስጦታዎች መኖርና በሥነ-ሥርዓት አገልግሎት ላይ መዋል ብቻቸውን በቂ አይደሉም፤ ስጦታዎችና አገልግሎታቸው በፍሬ መለወስ አለባቸው።

ከመንፈስ ቅዱስ ስራዎች ውስጥ ጥምቀትና ሙላት የሚባሉት ከሌሎቹ ይልቅ አከራካሪና አወያይ በመሆናቸው እነዚህን ሁለት ነጥቦች ከሌሎቹ የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች ይልቅ ሰፋ አድርጎ መመልከት አስፈላጊ ነውና ጠለቅና ተንተን አድርገን እንያቸው።

## የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት

ካሪዝማውያን አስተማሪዎች የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከደኅንነት በኋላ የሚፈጸም ደኅንነትንም ሙሉ ወይም ፍጹም የሚያደርግ ልምምድና ዳግመኛ ግብረ ጸጋ ወይም ዳግመኛ ቡራኬ እንደሆነና ይህም በአንድ ወቅት የሚሆንና በልሳንና በሌሎችም ስጦታዎች ታጅቦ እንደሚፈጸም ያስተምራሉ። ይህ ጥምቀት እንዴት እንደሚፈጸም ግን የተለያዩ አስተማሪዎች የተለያዩ አሳቦችን ይሰነዝራሉ፤ ማለትም በሥርዓተ ጥምቀቱ እንዴት መሆን ሁሉም ሙሉ በሙሉ አይስማሙም። አንዳንዶቹ አጥብቆ መፈለግ መታዘዝ፥ መጾም፥ መጸለይ፥ ባዶ መሆን፥ ንስሃ መግባት፥ መንጻት፥ መጠበቅ፥ ዋጋ መክፈል ወዘተ. አስፈላጊዎች መሆናቸውን አበክረው ያስተምራሉ። ብዙ ጊዜ እጅ ተጭኖና እንደ ዋና ምልክት ተደርጎ የሚወሰደው በልሳን መናገር እስኪፈጸም ድረስ

ሳያቋርጡ ይጸለያል። ምልክቱ በዕለቱ ካልተከሰተ ጸሎቱ በሌላ ጊዜ ይደረጋል። የሚጸለይለትም ሰው ንስሃ እንዲገባ ይበልጥ ዝግጅት እንዲያደርግና የመሳሰሉት ይነገሩታል። አንዳንድ ጊዜ እርስ በርስ የሚጋጩ አሳቦች ይሰነዘራሉ። በአመዛኙ ግን ግለሰባዊ ልምምዶች ከነባራዊው መለኮታዊ ቃል በላይ ዘልለው ቃሉም ተሸፍኖ ልምምዱ ሲያይልና ሲበረታ ይስተዋላል።

የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከደኅንነት በኋላ የሚሆን ክርስቶስ ያስቀረው ያልሞላ ደኅንነት ማሟያ ነው? ይህ እውነት ከሆነ የዳነና ይህንን 'ቡራኬ' ያልተቀበለ ሰው ደኅንነቱ ደኅንነቱ ይባላል? ለመሆኑ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ዓላማው ምንድን ነው? አንድ አማኝስ በመንፈስ ቅዱስ የሚጠመቀው መቼ ነው? አጥማቂውስ ማን ነው? እነዚህን አሳቦች ከአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ገጾች መመልከቱ አስፈላጊ ነውና ቃሉ የተጠቀሰባቸውን ቦታዎች በመግለጥ እንመርምር።

በሐዋ.2 የሆነውን ክስተት አዲስ ኪዳን በተለያዩ ቃላት ይገልጠዋል። ጥምቀት ይለዋል (ሐዋ.1:5 በዚህ ክፍል በተጨማሪ አብ የሰጠው ተስፋ እንደሆነ ተነግሯል)፥ ሙላት ይለዋል (ሐዋ.2:4)፥ መውረድ ይለዋል (ሐዋ.1:8) የዚህ መውረድ ውጤት ኃይልን መቀበል ነው)፥ ኃይል መልበስ ተብሏል (ሉቃ.24:49 በዚህም ክፍል አብ የሰጠው ተስፋ እንደሆነም ተጠቅሷል።) በጥቅሉ በሐዋ.2 የሆነውን ክስተት ጥምቀት፥ መውረድ፥ ሙላት፥ ኃይል መልበስ ልንለው እንችላለን። ክስተቱ አንድና ልዩ ቢሆንም አዲስ ኪዳን በተለያዩ ቃላት ገልጦታል።

መንፈስ ቅዱስ በበዓለ ኀምሳ ዕለት "የሰራው ስራ" ልዩና ያልተደገመ የማይደገምም የትንቢት ፍፃሜ ነው። መንፈስ ቅዱስ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንደገና እንደ አዲስ ይምጣ ማለት "ክርስቶስ እንደገና ይወለድ"የማለትን ያህል አይቻልም፤ አንድም ሆኑ መጥቷል። በሐዋ.2 መጀመሪያ የተፈጸመው ክስተት በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ እንደተደገመ በመጽሐፍ ቅዱሳችን አልተዘገበም። እንደሚነጥቅ ነፋስ ያለ ኃይለኛ ድምጽና እንደ እሳት የተከፋፈሉ ልሳኖች ከዚያ በኋላ አልሆኑም ከዚህም በኋላ ይሆናሉ ብሎ መጠበቅ ተገቢ አይደለም። ካሪዝማውያን አስተማሪዎች ራሳቸውን ጴንጤቆስጣውያን ብለው እንደዚህ የሚጠሩበት ምክንያት የጴንጤቆስጤው ማለትም የበዓለ ኀምሳው ዕለት ክስተት በሙሉ ወይም ቢያንስ በከፊል በልዩ ቋንቋ መናገርን በተለይ ዛሬም እንደያኔው የሚደገም ወይም የሚደጋገም ልምምድ ነው ብለው ስለሚያስተምሩ ነው። በበዓለ ኀምሳ የሆነውን ነገር አዲስ ኪዳን በተለያዩ ቃላት መግለጡ ያ ልዩ ሁኔታ ለመጀመሪያ ጊዜ ከመከናወኑ ጋር የተያያዘ ነው። መንፈስ ቅዱስ ለመጀመሪያ ጊዜ በተለየና ከዚህ በፊት ባላደረገው መንገድ

የመጣበት ጊዜ ስለነበር በአንድ ጊዜ ድርብርብ ድርጊቶችን የፈጸመበት ዕለት ነበር፥ ያ ዕለት። በዕለቱ ከተፈጸሙት ድርጊቶች አንዱ ጥምቀት ማለትም የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው።

በሐዋ.1:5 "ዮሐንስ በውኃ አጥምቆ ነበርና እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ አለ" ተብሎ ተጽፏል። ከላይ ከፍ ብሎ ደግሞ በቁጥር 4 ላይ ደግሞ አብ የሰጠው ተስፋና ደቀ መዛሙርቱ ከራሱ ከኢየሱስ የሰሙት እንደሆነ ተጽፏል። የዚህን ተስፋ ቃል በስፋት የምናገኘው በዮሐ.14:15-26 እና ዮሐ.16:7-15 ነው። በዮሐ.7:38 ላይ ጌታ በእርሱ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ምንጭ ከሆዱ እንደሚፈልቅ ተናገረ። በቁጥር 39 ላይ ዮሐንስ የዚህን አባባል ምንነት ሲያብራራ ይህ በጌታ የሚያምኑቱ የሚቀበሉት መንፈስ ቅዱስ መሆኑን ተናገረ። በዚህ ጥቅስ የምናገኘው ሌላ አሳብ ይህ መንፈስ ገና እንዳልወረደና እንዲወርድ ኢየሱስ መክበር እንደነበረበት ነው። ኢየሱስ መከራን ከተቀበለ ከሞተ በ3ኛው ቀን ከተነሳና በ40ኛው ቀን ካረገ በኋላ በ50ኛው ቀን መንፈስ ቅዱስ ወረደ። የመንፈስ ቅዱስ መውረድ የጌታ መክበር ምልክትም ነው። ከዚያ ዕለት ጀምሮ ይህ ለሞተ መንፈስ ሕይወትን የሚዘራና አማኞች ዳግም እንዲወለዱ የሚያደርግ መንፈስ የአዲስ ኪዳን አካል የሆነችውን የቤተ ክርስቲያን ተግባሩን ጀመረ። በወረደም ዕለት ቤተ ክርስቲያን ተወለደች። ቤተ ክርስቲያን ማለት ሕንፃ ሳትሆን በአማኞች የተሰራች መንፈሳዊ አካል የክርስቶስ አካል ወይም የአማኞች ጉባዔ ወይም መንፈስ ቅዱስ የኖረባቸው ሰዎች ስብስብ ነች።

የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የተጠቀሰባቸው የአዲስ ኪዳን ጥቅሶች ብዙ ስላልሆኑ አንድ በአንድ መመልከቱ አስፈላጊ ነው። ይህ ቃል በአዲስ ኪዳን ሰባት ጊዜያት ተጠቅሷል። አራት ጊዜ በወንጌላት ሁለቴ በሐዋርያት ሥራ በመጨረሻም በቆሮንቶስ መልእክት አንዴ ተጠቅሷል። በወንጌላት ውስጥ የተጠቀሱት መጥምቁ ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ በተናገረው ትንቢት የተናገራቸው ናቸው።

1. ማቴ.3:11 "እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በእሳትም ያጠምቃችኋል።"

2. ማር.1:8 "እርሱ ግን በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል።"

3. ሉቃ.3:16 "እርሱ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል።"

4. ዮሐ.1:33 "በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ እርሱ ነው።"

በወንጌላት ውስጥ የሚገኙት እነዚህ አራቱም መጥምቁ ዮሐንስ ስለ መሲሁ ኢየሱስ በተናገረው የትንቢት ቃል ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቀው ኢየሱስ መሆኑን የመሰከረባቸው ጥቅሶች ናቸው። በሐዋርያት ሥራ ከምናገኛቸው ጥቅሶች የመጀመሪያው ጌታ የሰጠው የተስፋ ቃል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በቆርኔሌዎስ ቤት ስለሆነው ነገር ጴጥሮስ የሰጠው ዘገባና ምስክርነት ውስጥ ይገኛል።

5. ሐዋ.1:5 "እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ።"

ይህ ከተባለ ከጥቂት ቀናት በኋላ መንፈስ ቅዱስ ወረደ ትንቢቱ ሞላ ተስፋውም ተፈፀመ።

6. ሐዋ.11:16 "እናንተ ግን በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ ያለው ትዝ አለኝ።"

ይህ የሆነበትን ሁኔታ በሐዋ.10:44-48እናገኛለን። እነዚህ ከአህዛብ ወገን የሆኑት ሰዎች መንፈስ ቅዱስን ስለተቀበሉ (ወይም ስለተጠመቁ) የመንፈስ ቅዱስ ስጦታም ስለፈሰሰላቸው ጴጥሮስ መንፈስ ቅዱስን ስለተቀበሉ በውሃ ደግሞ እንዲጠመቁ አዘዛቸው። በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ የክርስቶስ አካል ክፍል የመሆን ዋናው ውስጣዊ እውነት ሲሆን በውሃ መጠመቅ ደግሞ ውጪያዊው የእምነት መግለጫ ምልክት ነው።

የመጨረሻው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የተጠቀሰው በጳውሎስ ነው።

7. 1ቆሮ.12:12-13 "አካልም አንድ እንደሆነ ብዙም ብልቶች እንዳሉበት ነገር ግን የአካል ብልቶች ሁሉ ብዙዎች ሳሉ አንድ አካል እንዲሆኑ ክርስቶስ ደግሞ እንዲሁ ነው። አይሁድ ብንሆን የግሪክ ሰዎችም ብንሆን ባሪያዎችም ብንሆን ጨዋዎችም ብንሆን እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናልና። ሁላችንም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል።" ይህ ጥቅስ የመንፈስ ቅዱስን ትርጉም በግልጽ የምናገኝበት ክፍል ነው። እስካሁን ትንቢቶቹን፥ እውነታውንና በአንድ ቦታ ደግሞ መከሰቱን ብቻ ነበር ያየነው። እዚህ ግን የዓላማውን ምንነትና ትርጉሙን ነው የምናገኘው። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለምን አስፈለገ ብለን ብንጠይቅ መልስ የሚሰጠን ግልጽ ጥቅስ ይህ ነው።

ይህ ጳውሎስ የሚናገርለት ጥምቀት በበዓለ ኀምሳ ዕለት የተፈጸመው ብቻ ያለመሆኑ ግልጽ ነው። ምክንያቱም በዚያን ዕለትና በዚያ ጉባዔ የቆሮንቶስ

ምዕመናን በሙሉ አልነበሩም፤ ጳውሎስ እራሱም አልነበረም። ነገር ግን እዚህ ላይ ጳውሎስ እያስተማረ ያለው እውነት ይህ ጥምቀት በበዓለ ኀምሳው ዕለት ከተፈፀመው የመንፈስ ቅዱስ መውረድ ድርጊት የተነሳ ሊያገኙ የቻሉት አካል የመሆን በረከት ነው። እነዚህ ብዙ አስቸጋሪ ነገሮች ባሉባት ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ ምዕመናን መንፈስ ቅዱስን ተቀብለዋል ወይም ተጠምቀዋል ያንንም አንድ መንፈስ ጠጥተዋል። ይህ ጥቅስ ነጠላና ብዙ በሆኑ ቃላት ድርና ማግ የተሰራ ይመስላል። አንድ አካል፥ አንድ መንፈስ፥ ብዙ ብልቶች ብዙ ሰዎች። "እኛ ሁላችን" የሚለውን ብዛትን የያዘ አሳብና አንድ አካልና አንድ መንፈስ የሚሉት ነጠላ አሳቦች በማስተዋል ጎን ለጎን የተደረጉ ናቸው። በዚህ ምዕራፍ በጠቅላላው የምናገኘው አንድ ደማቅ አሳብ ይህ ነው።

በ1ቆሮ. 12:13 እንደምናየው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ጥቂቶች የታደሉትና ሌሎች ደግሞ ያተነፈጉት የመከፋፈያ ግድግዳ ሳይሆን አማኞች ሁሉ የታደሉት ልምምድ ነው። አማኞችም ሁሉ ወደ ክርስቶስ አካል የገቡበት መንገድ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከደኅንነት በኋላ የሚመጣ ወይም ተፈልጎ የሚገኝ ደኅንነትን የሚያሟላ የጥቂቶች ቡራኬ ሳይሆን ወደ ክርስቶስ አካል ማለትም ወደ ቤተ ክርስቲያን የመግቢያ ሥርዓትና የሁሉም አማኞች በረከት ነው።

ጂ.አር.ደብልዩ. እስቶት የተባለ የመጽሐፍ ቅዱስ መምህር መንፈስ ቅዱስን መቀበልና በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ አንድና ያልተለያዩ የአዲሱ ኪዳን በረከት መሆናቸውን ከተናገረ በኋላ እንዲህ ብሏል፤

> የእግዚአብሔር ዓላማ ህዝቡ ሁሉ የአዲሱ ኪዳን በረከቶች የሆኑትን የኃጢአት ይቅርታና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እንዲቀበሉና የውኃን ጥምቀት እንደ ምልክት በመቀበል እነዚህን በረከቶች እንዲያትሙት ነው። ከዚያ በኋላ ሳያቋርጡ በመንፈስ በመሞላት ይህን ሙላት በተቀደሰ ሕይወትና ድፍረት ባለው ምስክርነት መግለጥ ነው። በዕብራውያን መልእክት ውስጥ ክርስቲያኖች በሙሉ ከመንፈስ ቅዱስ ተካፋዮች የሆኑና ሊመጣ ያለውን የዓለም ኃይል የቀመሱ ተብለዋል። (ዕብ.6:4-5) እንደ አዲስ ኪዳን አባባል በመንፈስዳግም ከመወለድ በኋላ ያለው የክርስቲያን ሕይወት በሙሉ መንፈሳዊ ወይም የመንፈስ ቅዱስ ሕይወት ነው።[4]

የቆሮንቶስን መልእክት በሙሉ ስንቃኘው ትምህርታዊ መልእክት ሳይሆን ተግሳፃዊ ወቀሳና የጥያቄዎች ምላሽ ነው። በዚህ ክፍል የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ተጽፎ የምናገኝበት ምዕራፍ የአካል አንድነት የተጻፈበት ምዕራፍ

ነው። ቀደም ካሉት ምዕራፎች በጥቂቱ ስለ መለያየትና ስለ መከፋፈላቸው አውስቶ በሰፊው ተናግሯል። በዚህ ክፍል ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን በአካል በመመሰል ስለ አንድነት ነው የሚናገረው። ጳውሎስ አካልን የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ በማድረግ ደግሞ ደጋግሞ መልእክቶችን አስተላልፏል። ለምሳሌ ሮሜ.12፤ 1ቆሮ.10፤ ኤፌ.1 እና 2 በተለይም 4 ላይ ይህን ምሳሌ ደጋግሞ ተጠቅሟል። በዚህ በ1ቆሮ.12:12-27 ባሉት 16 ጥቅሶች ውስጥ ብቻ እንኳ 18 ጊዜያት ይህ "አካል" (ወይም በግሪክ ሶማ) የተባለው ቃል ተጠቅሷል። እግዚአብሔር ምን ሊያስተምረን መፈለጉ ከግልጽም በላይ ነው። አካል በአስገራሚ ሁኔታ ብዙ ብልቶች ያሉት በዚያኑ ያህል አስገራሚነት ደግሞ አንድ የሆነ ነገር ነው። አንድም ብዙም። ቤተ ክርስቲያንም ከዚህ የተለየች አይደለችም። ቤተ ክርስቲያን በህያዋን ብልቶች የተሰራች ሕያው ዘአካል (organism) ናት። በትናንሽ ስብርባሪ አካላት የተሰራች ሳትሆን በብልቶች የታነጸች አካል ናት። ስጦታዎች ብዙ ቢሆኑም አካል ግን አንድ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ይህ አንድ አካል የተሰራበት መንገድ ወይም ብልቶች የአካሉ ክፍል የሆኑበት መንገድ ነው።

የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሲወሳ አጥማቂው መንፈስ ቅዱስ ሳይሆን ክርስቶስ መሆኑ መታለፍ የሌለበት እውነት ነው። አንድ ዕውቅ ጸሐፊ ስለዚህ ርዕስ ሲጽፍ፤

> ዮሐንስ ክርስቶስ ከእርሱ በኋላ መጥቶ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ስለማጥመቁ በተናገራቸው ሁለት ክፍሎች ተመሳሳይ ቃላት እናገኛለን፤ ማር.1:7-8 እና ሉቃ.3:19። ልክ በዮሐ.1:33 ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ 'በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ እርሱ ነው' እንዳለው ሁሉ በሁሉም ቦታ አጥማቂው እንደሆነ በግልጽ የተጠቀሰው ኢየሱስ ነው።
>
> በጴንጤቆስጤው ቀን ስብከቱ ጴጥሮስ ስለ ክርስቶስ እንዲህ አለ። 'ስለዚህ በእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ ብሎና የመንፈስ ቅዱስን የተስፋ ቃል ከአብ ተቀብሎ ይህን እናንተ አሁን የምታዩትንና የምትሰሙትን አፈሰሰው' (ሐዋ.2:33) እርሱ በጴንጤቆስጤው ዕለት ተአምራት መንፈስን እንዳፈሰሰው በመንፈስም ያጠመቀው እርሱ መሆኑን እናያለን።
>
> መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቶስን ሁሌም እንደ አጥማቂው ይገልጠዋል። አጥማቂው ከቶውኑ መንፈስ ቅዱስ አይደለም። ብዙ ጊዜ ካሪዝማውያን አማኞች ሲናገሩ 'እኛ የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት አግኝተናል' ይላሉ። ይህን ሲሉም መንፈስ

> ቅዱስ ለእነርሱ የሆነን ነገር እንዳደረገላቸው ያስባሉ። ሲድኑ በክርስቶስ መጠመቃቸውን አሜን ብለው ይቀበሉ ይሆናል ይሁን እንጂ 'የመንፈስ ጥምቀት' ከዚያ በኋላ አጥብቀው ስለፈለጉት ያገኙት መሆኑን ደጋግመው ይናገራሉ። ስንመለከተው ግን መንፈስ ቅዱስ የማጥመቁን ሥራ አያከናውንም። መንፈስ ቅዱስ የጥምቀቱ አማካይ ነው። ልክ ዮሐንስ በውሃ እንዳጠመቀ እኛን በእግዚአብሔር መንፈስ አማካይነት ወደ አካሉ ያጠመቀን ክርስቶስ ነው። [5]

ከክርስቶስ እርገት በኋላ እስከ በዓለ ኀምሳ እለት ድረስ ሐዋርያት የመንፈስ ቅዱስን መውረድ እየጾሙና እየጸለዩ ለአሥር ቀናት እንደጠበቁ ከበዓለ ኀምሳ እለት በኋላ ለመጠመቅ መጠበቅ አላስፈለገም። ከሐዋ.2 በኋላ መንፈስ ቅዱስ እንዲወርድ ሲጠበቅ አናገኝም። የመጀመሪያዎቹም የጠበቁበት ምክንያት እንዲጠብቁ ስለታዘዙና ተስፋውም ስለተሰጣቸው ነበር። ከበዓለ ኀምሳ በኋላ ላመኑት መንፈስ ቅዱስ የሚጠበቅ ተስፋ መሆኑ አቆመ። በዘመናችን አንዳንዶች ባለማስተዋል ለ10 ቀናት ብቻ ሳይሆን ለሳምንታት ለወራትና ለዓመታትም በመንፈስ ቅዱስ ለመጠመቅ የሚጠብቁ አሉ። የጠበቁትና የፈለጉት ልምምድ ካልተፈጸመ ተስፋ የሚቆርጡና እግዚአብሔር ለእነርሱ የማይገደው አምላክና የማይፈልጋቸውም የመሰላቸው አያሌ ናቸው። የሚያገለግሉትን አገልግሎት በቅንነትና በታማኝነት እያገለገሉ ሳሉ ጎዶሎነታቸው ተነግሯቸው አገልግሎታቸውን ያለ መንፈስ ቅዱስ ኃይል እያገለገሉ እንደሆነ ስለተባሉና ስለመሰላቸውም "በራሴ ጉልበት ከምንገታገት ቢቀርብኝስ" እያሉ ማገልገል ያቆሙና እንዲያውም በሚያሳዝን ሁኔታ የሕይወት መንገድ ከሆነው ክርስትናም ያፈገፈጉና ገሸሽ ያሉም በርግጥ አሉ። እነዚህ አማኞች ሕይወታቸውን እንዲመለከቱ የተደረጉት እንደደረቀ እንጨት፥ እንደሚንኳኳ ቆርቆሮ፥ ፊደል ብቻ የሚናገሩ እንጂ መንፈስ እንደሌላቸው፥ ፊደል ደግሞ እንደሚገድል፥ በመንፈስ ቅዱስ እንደማያምኑና እንዲያውም መንፈስ ቅዱስን እንደሚቃወሙ ወይም በኃጢአታቸው ምክንያት እንዳሳዘኑትና እርሱም ለማጥመቅ እንቢ እንዳላቸው ነው። መንፈስ ቅዱስን ያለማመን ማለት መንፈስ ቅዱስ የሥላሴ አካል የሆነ አምላክ ነውና በእግዚአብሔር ያለማመን ማለት ነው። አንድ ሰው በመንፈስ ቅዱስ የማያምን ከሆነ ጨርሰውኑ አልዳነም ማለት ነው፤ ምክንያቱም የምንድነው በጸጋው በእግዚአብሔር እምነት አማካይነት ነው። ከዳነ ደግሞ አንድ አማኝ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ዳግም የተወለደ የእግዚአብሔር ልጅ ነውና ይህን ልጅነቱን የሚመሰክርለት መንፈስ በውስጡ መኖር ጀምሯል ማለት ነው።

አንድ አማኝ ሲድን ወዲያውኑ ከመንፈስ ቅዱስ ተወልዷል። (ዮሐ.3:5-6) ገላ.4:6 ደግሞ "ልጆችም ስለሆናችሁ እግዚአብሔር አባ አባት ብሎ

የሚጮኽ የልጁን መንፈስ በልባችሁ ላከ።" ይላል። አንድ ሰው ሲያምን መንፈስ ቅዱስ ያን ሰው ሊመራው ጀምሯል ማለት ነው። ከመንፈስ ቅዱስ ተግባሮች አንዱ በክርስቶስ የሚያምኑትን ወደ እውነት መምራት ነው። ሮሜ.8:14-16 እንዲህ ይለናል፤ "በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና። አባ አባት ብለን የምንጮህበትን የልጅነት መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ እንደገና ለፍርሃት የባርነትን መንፈስ አልተቀበላችሁም። የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል።" የእግዚአብሔርን መንፈስ የተቀበሉ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው፤ ልጆች የሆኑም ሁሉ የእግዚአብሔርን መንፈስ (መንፈስ ቅዱስን) ተቀብለዋል። አንድ ሰው የክርስቶስ መንፈስ ሳይኖረው የክርስቶስ ወገን መሆን እንዴት ይችላል? ይህ ከቶ የማይሆን ነው። (ሮሜ.8:9)

ይህ መንፈስ አማኙ በዳነበት ቀን መጥቶ በእርሱ መኖርን የሚጀምር እንጂ ትንሽ በትንሽ እና እየተጠበቀ የሚመጣ አይደለም። እግዚአብሔር መንፈሱን እየሰፈረና እየለካ የሚሰጥ አምላክ አይደለም። በሐዋርያት ሥራም ሆነ በመልእክቶች ውስጥ የትኛዋም ቤተ ክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስን መምጣት ስትጠባበቅ አናይም። የዳኑ አማኞችም ለመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ዳግመኛ አቀባበል ሲያደርጉ አናነብም። እንዲህ የመሰለው ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቢሆን ኖሮ ቅዱስ ቃሉ ገልጦ ባስቀመጠው ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረውን እንደምናከብር ሁሉ ዝም ቢል እንኳ ዝምታውን ማክበር አለብን እንጂ በዝምታው ቦታ የመሰለንን ወይም የግምታችንን መሳግና በመስመሮቹም መካከል የራሳችንን አሳብ ማንበብ የለብንም። ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀትም ቢሆን በግልጽና በበቂ ሁኔታ ተጽፏል። ይህ ነገር ማለትም የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከተዳነ (ከደኅንነት) በኋላ የሚገኝ ልምምድ ቢሆን ኖሮ መጽሐፍ ቅዱስን እንዲጻፍ ያደረገው መንፈስ ቅዱስ እራሱ በየዘመናቱ ሁሉ እንደ አዲስ እንደሚመጣ በተናገረ ነበር።

ከበዓለ ኀምሳ ወዲህ አዲስ ስርዓት ነው የሆነው። አንድ አማኝ ባመነበት ቅጽበት የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ መሆን ጀምሯል እንጂ መንፈስ ቅዱስ መጀመሪያ መጥቶ የሚኖርበትን ቤት አይቶ ወይም አጽድቶ ከሄደ በኋላ ሁለተኛ ጊዜ ጓዝጓዙ ሊቀመጥ ጓዙን (ስጦታዎችንና ሌሎችም በረከቶችን) ይዞ ለዘለቄታው ሊኖርበት አይመጣም። 1ቆሮ.6:19 "ወይስ ስጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ አታውቁምን? ይላል። "የተቀበላችሁት" የሚለው ስጋቸውን ሳይሆን መንፈስ ቅዱስን መሆኑ ይታያል። እነዚህ በሰፊው ሲታዩ ስጋውያን የሆኑ የቆሮንቶስ ምዕመናን እንኳ የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆኑ ተነግሮላቸዋል። ይህ መንፈስ በውስጣቸው መኖር ከጀመረ በኋላ በእርሱ

ቁጥጥር ስር መሆናቸውን ትተው በፈቃዳቸው መመላለስ ጀመሩ እንጂ ሲያምኑስ በእርግጥ የእርሱ መኖሪያ መሆን ጀምረዋል። ለሚቀድሰው አሰራሩ ራሳቸውን አይሰጡና አይደጉ እንጂ መጠመቅስ ተጠምቀዋል። እንዲህ ካልሆነማ አንድ ሰው ዳግም ተወልዶ በመንፈስ ቅዱስ 'ተጠመቀ' እስከተባለበት ጊዜ ድረስ መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ዘንድ የለም፣ የእግዚአብሔር ወገንም አይደለም ወይም በሌላ አነጋገር ጨርሰውኑ አልዳነም ሊባል ነው።

አንድ ሰው በመረዳትና ኃጢአተኛነቱን በመገንዘብ ራሱን ለእግዚአብሔር ከልብ በሆነ እምነት ሲሰጥ ማለትም ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን መድኃኒቱና የሕይወቱ ጌታ ለማድረግ ሲወስን እግዚአብሔር እንደ ልጅ ይቀበለዋል። መንፈስ ቅዱስም በእርሱ መኖር ይጀምራል፤ በእርሱ ውስጥ መኖርን ከመጀመሩ የተነሳ ውስጣዊ ለውጡ ጎልቶ በውጪያዊ ባህርዩም መታየት ይጀምራል። ፍጹም የሆነ የአኗኗር ጥራት ያላቸው ለውጦች በሕይወቱ ከመታየታቸውም አልፎ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ በእርሱ ይታያል። በተጨማሪም ልዩ የሆኑት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች መድመቅና መታየት ይጀምራሉ። እያንዳንዱ አማኝም ቢያንስ አንድ የጸጋ ስጦታ ታድሏል። ስጦታም የሌለው አማኝ የለም። ይህን የሚያድለውና ምንን ለማን መስጠት እንዳለበት የሚወስነው መንፈስ ቅዱስ ራሱ እንጂ ሰዎች አይደሉም። እንደ ብፌ ምግብ እየቀነጣጠቡ መውሰድ ወይም መርጦ መስጠትም ሆነ መርጦ መቀበል ማንም አማኝ አይችልም። የስጦታዎቹ ባለቤት በአማኙ ውስጥ ኑሮውን መኖር የጀመረው መንፈስ ቅዱስ ነው።

መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ውስጥ ሆኖ ልጅነቱን ከአማኙ መንፈስ ጋር እንደሚመሰክር በሮሜ.8:16 ተጽፏል። ከአማኙም ምስክርነት ይልቅ የጸናው ምስክርነት ደግሞ ዘመናት የማይሽሩትና በሰዎች ልምምዶችም ላይ ባለ ስልጣን ሊሆን የሚገባው ንጹሑ የእግዚአብሔር ቃል ምስክርነት ነው። ከኛ ምስክርነት ይልቅ የቃሉ ምስክርነት ማየል ያለበት ምክንያት የኛ ምስክርነት በስሜታችን ሊደበዝዝ ስለሚችል ነው። ስሜቶቻችን ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል አሜን ብለው መቀበል አለባቸው እንጂ ቃሉ የሚናገረው እውነት ለስሜታችን ስላልተሰማው የግል ማረጋገጫ መፈለግ ወይም ደግሞ በግድ እንዲሰማው ሰው ሰራሽ የሆነ እርግጠኛ የሚያደርገንን ነገር መፍጠር የለብንም።

## የመንፈስ ቅዱስ ሙላት

አንድ ጊዜ ሁለት የቤተ ክርስቲያን ጓደኞቼ (ወንድና ሴት ናቸው) አብረው ሆነው ስለተለያዩ ርዕሶች እየተጨዋወቱ ይህን የመንፈስ ቅዱስ ሙላት የተባለውን ርዕስ ያነሱታል። ሰውዬው ከዚህ በፊት የአንድ ክርስቲያን በመንፈስ

ቅዱስ መሞላት ምልክቱ በልዩ ልሳናት መናገሩ እንደሆነ ያስተማሩትን ትምህርት በመቀበሉ በብዙ ጉባዔዎች እየተገኘ ተጸልዮለታል። ሬይንሀርድ ቦንኬ ባገለገለበት አንድ ስብሰባ ላይም ተገኝቶ ከጀማው ጋር ተጸልዮለት ነበር። ባለቤቱም ከእርሱ የበለጠ ጥረት አድርጋ ነበር። በኋላ ግን እርሱና ባለቤቱ ኮስተር ብለው የእግዚአብሔርን ቃል ሲመረምሩ የተሳሳተ መንገድ ላይ መሆናቸውን ማለትም የእግዚአብሔር ቃል ይህ ስጦታ እንዳይከለከል እንጂ እየተሳደደ እንዲፈለግ እንደማይናገር ተረድተውና ባላቸውና በተሰጣቸው ነገር በጌታ ረክተው በየመስመራቸው በቤተ ክርስቲያናቸው እያገለገሉ ያሉ ባልና ሚስት ሊሆኑ በቅተዋል።

አሁን ከዚህ ወንድም ጋር ስለዚህ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት የምትነጋገረዋ እህት ደግሞ በዚህችው ቤተ ክርስቲያን ጌታን የምታመልክና የምታገለግል እህት ስትሆን ከዚህ በፊት በነበረችባቸው ቤተ ክርስቲያኖች የተሰጣት ትምህርትና የተቀደደላት ፈር የመንፈስ ቅዱስ ሙላትና ልሳን የሳንቲም ጎፈርና ዘውድ (የአንድ ሳንቲም ግልባጭ) እንደሆኑ ነበር። ይህን ጭውውት ባደረጉ ሰሞን ይህች እህት በሌሎች ሦስት የተለያዩ ቦታዎች ሦስት የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ያዘጋጁትን ኮንፍራንሶች ስትካፈል ሰንብታ ነው የተመለሰችው። በኮንፍራንስ ማግስት የሰንበት አገልግሎት እንኳን ከሌላ ቦታ ሲሟሟቅ ከርሞ ለመጣ ሰው እዚያም ለሰነበተውም ቢሆን እንደሚቀዘቅዝበት የማይካድ እውነት ነው። ለዚህች እህት ቤተ ክርስቲያኗ ከቀድሞውም ይበልጥ አነሰባትና የምታመልክባት ቤተ ክርስቲያን ኃይል የሌለባት መንፈስ ቅዱስ የማይሰራባት አድርጋ ማማረር ጀመረች። ቀደም ሲል ከተጠቀሰው ወንድም ጋር እርሷ የገባችን እርሱም የደረሰበትን የሚነጋገሩት በዚህ ጊዜ ነበር።

"ላንቺ ምን ይመስልሻል ምልክቱ?" አላት። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ምልክት ማለቱ ነው።

"በልሳን መናገር አለበት ካልተናገረ መሞላቱ አይታወቅም" አለችው። ይህን ሰፋ አድርገው ተነጋገሩና

"አንተስ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ምልክቱ ምንድን ነው ነው የምትለው?" አለችው።

"በፍሬው ነው የማውቀው። ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም ሌሎችም የመንፈስ ፍሬ የተባሉት የሚታይበት ከሆነ ያ ሰው በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ነው። እንግዲያማ ስንቶች የማይተረጎም ልሳን እያንበለበሉ ባልተቀደሰ ኑሮ የሚደነባበሩ አሉ አይደል?" አላት።

"አዎን ልክ ነህ አንዳንዶች በመንፈስ ተሞልተው ግን ፍሬ የሌላቸው አሉ ግን አንዳንዶች ደግሞ መንፈሷ ሳይኖራቸው ፍሬ ያላቸው አሉ" ስትለው፤

"ዛፉ ሳይኖር ፍሬ አለ ማለትሽ ነው? ዝም ብሎ ምንም ነገር ያልያዘው አየር ላይ የተንጠለጠለ ፍሬ አለ ማለትሽ ነው?" አላት። ንግግራቸውን ከዚያ በኋላ ብዙም አልገፉበትም።

እግዚአብሔር ለኛ ለልጆቹ ያለው አንድ ውብና ውድ ዕቅድ እኛ ክርስቶስን እንመስል ዘንድ ነው። በሕይወታችን ፍሬያማ፥ በመንፈሳዊ ውጊያችን አሸናፊዎች፥ በአገልግሎታችንም ውጤታማና ስኬታማዎች እንድንሆን። በዚህም ሁሉ ደግሞ መንግስቱ እንድትሰፋ ቅዱሳን እንዲባረኩና እርሱም ራሱ እንዲከብር ይወዳል። ይህ ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው? እኛ እንደሆንን በራሳችን ጌታን የሚያስደስት ኑሮ እንኳን ሁሌ አንዴም አይቻለንም። ለዚህ ጥያቄ መልስ የሚሆነው በአማኞች ውስጥ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ህልውና ነው።

ጌታን ስንቀበል መንፈስ ቅዱስ በኛ ውስጥ መኖር ጀምሯል። ከኛ ጋር ሳይሆን በኛ ውስጥ ነው። በኛ ውስጥ ካልሆነ ከኛ በጣም ሩቅ ነው። በኛ ውስጥ ሲኖር ደግሞ ላይተወንና ሊኖርብን ነው። በኛ ውስጥ መኖሩ በራሱ ብቻውን የደኅንነታችን ማረጋገጫና የልጅነታችንም ምስክር ነው። ክርስትናን በተግባር ሚዳ ስንፈትነው ግን ይህ ብቻ በቂና የተጠራንለትን ዒላማ የሚመታ (ከግብ የሚያደርሰን) አይደለም። መንፈስ ቅዱስ በኛ ውስጥ ሲኖር እኛም በመንፈስ ልንኖርና ልንመላለስ በየዕለቱም ራሳችንን ለርሱ ልንሰጠው ይገባናል። ይህ የሚሆነው በመንፈስ ስንሞላ ነው።

ሙላትን ካሪዝማውያን በአንድ ወቅት የሚደረግ የተለየ ልምምድ አድርገው ነው የሚወስዱት። ምስክርነት ሲሰጡም 'በዚህ ቀን፥ በዚህ ሰዓት፥ በዚህ ቦታ' በመንፈስ ቅዱስ እንደተሞሉ ይናገራሉ። ምልክቱንም በሌሎች ልሳኖች መናገራቸውን ያደርጋሉ። በልሳኖች መናገርን እንደ መሞላት ምልክት ሳይሆን እንደ ጸጋ ስጦታ በሚመለከቱት ዘንድ ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት የአንድ ቀን ልዩ ልምምድ ሳይሆን በውስጣቸው ለሚኖረው ለመንፈስ ቅዱስ ባለማቋረጥ መሰጠት ወይም አምላክ ለሆነው ለመንፈስ ቅዱስ ለርሱ መገዛት ነው። ምልክቱም በአማኙ ሕይወት ውስጥ የሚታየው የሰከነ፥ አሸናፊ፥ የተቀደሰና በፍሬ የተሞላ ሕይወት እንዲሁም ታማኝነትን የተሞላ አገልግሎት ነው። ኤፌ.5:18 በመንፈስ ማለትም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ ሲለን ሦስት ዋና ዋና አሳቦች እንዳሉበት መስተዋል አለበት።

- የመጀመሪያው መሞላት ትዕዛዝ መሆኑ ነው። ይህ ቃል ልመና ወይም አስተያየት ወይም የወደደ ሊቀበለው ያልወደደ ሊተወው የተሰነዘረ አሳብ አይደለም። ትዕዛዝ ነውና ሁሉ ሊሆኑ ማለትም ሊሞሉ ይጠበቅባቸዋል፤ የምርጫ ጉዳይና የፍላጎት ማለትም ካልፈለጉ የሚተዉት ነገር አይደለም። ልክ 'አትግደል' እንደሚል ትዕዛዝ ይህም ትዕዛዝ ነው።

- ሁለተኛው ለአማኞች ሁሉ የተሰጠ ትዕዛዝ ነው። እኒህ የኤፌሶን አማኞች በሙሉ የዳኑና በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቁ ማለትም የክርስቶስ አካል ብልት የሆኑ ናቸው። (ኤፌ.1:1 እና 1ቆሮ.12:13) ለተወሰኑ ምዕመናን የተነገረ ሳይሆን ለሁሉም የተባለ ነው።

- ሦስተኛው ደግሞ መሞላት ሳያቋርጡ በቁጥጥር ሥር መሆን ማለት ነው። በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር መሆን በጌታ ጌትነት ስር መሆን ማለት ነው። መንፈስ ቅዱስ እኛ የምንጠቀምበት ኃይል ወይም ጉልበት ሳይሆን እኛ ልንኖርለትና ሊገዛን የሚወድ አምላክ ነው።

በመንፈስ ቅዱስ መሞላት እያንዳንዱ ክርስቲያን የታዘዘውና የሚጠበቅበትም ኃላፊነት ነው። አንድ አማኝ ከመንፈስ ቅዱስ ከመሞላት ያነሰ ወይም የጎደለ ኑሮ እየኖረ ከሆነ የሚጠበቅበትን ወይም እግዚአብሔር ሊኖር የሚፈልግበትን ኑሮ እየኖረ አይደለም ማለት ነው። በኤፌ.5:18 "መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ ይህ ማባከን ነውና" ይላል።

በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ማለት በእርሱ ማለትም በመንፈስ ቅዱስ ሙሉ ቁጥጥር ስር መሆን፥ በእርሱ መገዛት፥ በእርሱ መሸነፍ ማለት ነው። ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ መሞላትን በወይን ጠጅ ከመስከር ጋር ነው ጎን ለጎን ያስቀመጠው። ይህ ማለት የወይን ጠጅ አስክሮ ከአእምሮ ውጪ የሆነ ስራ እንደሚያሰራ መንፈስ ቅዱስም እንደዚያ ያስደርጋል ማለት አይደለም። እንዲያውም ተቃራኒ የሆኑ ሁለት አሳቦችን ነው አብሮ በማስቀመጥ እያስረዳ ያለው። እነዚህ ነገሮች በመሠረቱ ተቃራኒ መሆናቸውን "ይህን አድርጉ ያኛውን አታድርጉ" ከሚለው አሳብ መረዳት አያዳግተንም። አንዳንድ አስተማሪዎች ይህን ጥቅስ በተሳሳተ መስመር በማስኬድ የወይን ጠጅን እንደ ስጋዊ የመንፈስ ቅዱስን ደግሞ እንደ መንፈሳዊ ስካር አስመስለው ያስተምራሉ። አንዳንዶችም ከአእምሮ ውጪ የሆኑ ጤናማ ያልሆኑ ድርጊቶችን ቢፈጽሙ ጤናማ እንደሆኑና በመንፈስ "ሰክረው" ያደረጉት እንደሆነ በመቁጠር እንግዳ ስራቸውን ያጸድቁላቸዋል። በሐዋ.2 ሐዋርያትም ጉሽ የወይን ጠጅ ጠጥተው እንደሰከሩ

ያህል እንደተቆጠሩ ይጠቅሳሉ። በበዓለ ኀምሳ እለት የተደረገው እንግዳ ነገር እንኳንስ የሰከረ ሙሉ ጤና ያለውም ሰው ቢሆን የሚያደርገው አልነበረም። እስኪ ማነው እንኳንስ ሰክሮ በጤናውስ ቢሆን ከዚህ ቀደም ባልተማረው ወይም በማያውቀው ቋንቋ የጌታ እግዚአብሔርን ድንቅ ስራ በህዝብ ፊት የሚናገር?

ጳውሎስ በዚህ ቦታ ላይ የወይን ጠጅን ከመንፈስ ጋር ለማነጻጸር የተጠቀመበት ምክንያት በወይን ጠጅ የተሞላ ሰው በወይኑ ጠጅ ቁጥጥር ስር የዋለ የእርሱ ተገዢ መሆኑን ለማሳየት ነው። ይህ ሰው በጤናማ አዕምሮ የማያደርጋቸውን ሥራዎች በዚህ ጊዜ ይሠራል። በውስጡም የተደበቀውንና ሆዱ ያባውን ሁሉ ያወጣዋል። ሙላትን ከስካር ጋር ማመሳሰል ትክክል አይሆንም እንዲያውም ከመንፈስ ቅዱስ አሰራር ጋር የማይገናኝና የማይመሳሰል ንጽጽር ነው። በበዓለ ሃምሳ ቀን 'ሰከሩ' ያሏቸው ያፌዙባቸው ሰዎች ነበሩ እንጂ ጸሐፊው ሉቃስ አልነበረም። መንፈስ ቅዱስ እኛን ከአዕምሯችን ውጪ አድርጎ እንደ ዕቃ የሚጠቀምብን የዕቃ ባለቤት ሳይሆን የከበረ ሆኖ የተከበረን ሥራ የሚሰራ አምላክ ነው።

አንዳንድ 'በመንፈስ ቅዱስ የተሞላን ነን' የሚሉ አማኞች ከአግባብ ውጪ በሚሆኑበት ጊዜ ለምን? ተብለው ሲጠየቁ 'እኔ ምን እንዳልኩ፥ ምን እንደተናገርኩ፥ ምን እንደሆንኩም አላውቅም! እርሱ እራሱ ነው...' በማለት በመንፈስ ቅዱስ ያሳብባሉ። በ170 ዓ.ም. አካባቢ የሞንታኖስ ትምህርት በተጀመረ ጊዜ የፈጠረው አንዱ ውዝግብ ሞንታኖስና ተከታዮች መንፈስ ቅዱስ በነቢይ አድርጎ ሲናገር አማኙ ዕቃ የሆነ ያህል መተላለፊያ ብቻ መሆን አለበት፥ በአዕምሮው መሆን የለበትም፥ በአዕምሮው ከሆነ የሚተላለፈው መልእክት ሊረከስ ይችላል የሚል ትምህርት ሲያስተምሩ በጊዜው የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ደግሞ እውነተኛ ነቢይ በሙሉ አዕምሮውና ስሜቶቹ በመሆን ምንም ዓይነት መንቀጥቀጥና መርበድበድ ሳይታይበት መናገር እንዳለበት አበክራ አስተምራለች።[6] ይህ በጊዜው ሞንታኒዝም ወይም ፍርግያዊው ሃሳዊ ትምህርት እየተባለ የሚታወቀው በሁለተኛው መቶ ምዕተ ዓመት የነበረ ትምህርት ሲሆን ልምምዱ ግን ለዘመናችን ክርስትናም እንግዳ ያልሆነ ትምህርት ነው።

ጳውሎስ ሙላትን ከስካር አነጻጽሮ መጥቀሱ እየተንገዳገዱ ከመውደቅ ጋር ለማመሰል ሳይሆን ለመንፈስ በመገዛት የሚደረግ አገልግሎትን መናገሩ ነው። አንዳንዶች ይህንን ጥቅስ እንዳሻቸው በመረዳት ከሰካራም ያላነሰ ከክርስትና መስመር የወጣ ሥራ እንደሚሰሩ ይታያል። ሙላት እንደ ባለውቃቢ መጨፈር፥ እንደ ባለዛር መጮህ፥ እንደ አዶከብሬ መግዘፍ አይደለም። መንፈስ ቅዱስ እሽክርክሪት እንደሚጫወት ልጅ አሽከርክሮ የሚደፋ ወይም

እንደ አዙሪት አጥመልምሎ የሚጥል አይደለም። መንፈስ ቅዱስ ልብስን የሚያስቀድድ፥ ዕርቃንን የሚገልጥ፥ ዕቃን የሚያሰብር፥ አካልን ከዕቃ ጋር የሚያላጋ ሳይሆን ከባህርዩ ጋር የሚጣጣም ጨዋ ስራን የሚሰራ ጨዋ አምላክ ነው። እርሱ ቅዱስ መንፈስ ነው!

በእርግጥ መንፈስ ቅዱስ ምንም እንኳን በመንፈሳችን የምንረዳው አምላክ ቢሆንም ኀልውናውን በስሜት ኀዋሳታችን እንዲሰማን ሊያደርግም ይችላል። ይህ ስሜት ደስታና ሐሴት ማድረግን በሚያስጠብብ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ፍጹም በሆነ መጽናናት መጽናናትን፥ ከኃጢአትና ከበደል የተነሳ መቆጨትና ማዘንን ወይም ከውለታና ከመደሰትም የተነሳ ማንባትን እንዲሁም የመሳሰሉትን ሊያንጸባርቅ ይችላል። ሆኖም ስሜት ገንኖ የበላይ ይሆንና አዕምሮ ተሸፍኖ በስሜት ብቻ ከተቆየ የሕፃን ስራ መሰራቱ የማይቀር ነው። ጳውሎስ በ1ቆሮ.14:20 ላይ የጻፈልን ደግሞ ለክፋት ነገር ብቻ ካልሆነ በቀር በአዕምሮ የበሰልን እንድንሆን ነው።

የአዲስ ኪዳን ግሪክ ቋንቋ ምሁር የሆነው ኬነት ዉስት በኤፌ.5:18 በተለይም 'ይሙላባችሁ' ስለሚለው ቃል ሲጽፍ፥

> ይሙላባችሁ ማለትም ፕሌራኦ እስከአፍ መሙላት፥ ማብዛት፥ አበርክቶ ማቅረብ፥ ማጉረፍ፥ በሙላት ማሠራጨት ማለት ነው። በሐዋ.6:15 በእምነትና በመንፈስ ቅዱስ የተሞላውን እስጢፋኖስን እናያለን። እምነት እስጢፋኖስን የሞላው በመቆጣጠር መልክ ነበር። መንፈስ ቅዱስም እስጢፋኖስን ሞላው ስንልም ተቆጣጠረው ማለታችን ነው። ስለዚህ የመንፈስ ሙላት ለእርሱ ራሱን የሰጠውን አማኝ መቆጣጠሩን ያመለክታል። ግሱ የአሁን ጊዜና ትዕዛዛዊ ሲሆን ባለማቋረጥ በመንፈስ እየተሞላችሁ ኑሩ የሚል ነው። ትርጓሜውም 'ሳታቋርጡ አሁንም አሁንም በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር ሁኑ' ማለት ነው።[7]

ይህ ሙላት የማያቋርጥ ሙላት ነው ማለት ነው እንጂ እንደ ክትባት አንዴ ወስደነው ከዚያ ወዲያ በቃኝ የምንለው አይደለም። ያለማቋረጥ መፍለቅ፥ መውረድ፥ መፍሰስ ያለበት ሙላት ነው።

ይህ ሙላት በዮሐ.4:13-14 እንደምናነበው ጌታ ሳምራዊቱን ሴት ባገኘ ጊዜ ከዚያ ከያዕቆብ ጉድጓድ የሚወጣውን ውሃ የሚጠጣ ዳግመኛ እንደሚጠማ እርሱ ከሚሰጠው ውሃ የሚጠጣ ግን የዘለዓለም ሕይወት ውሃ ምንጭ ከሆዱ ስለሚፈልቅ ከቶ እንደማይጠማ እንደተናገረው ዓይነት ነው። በተጨማሪም

ጌታ በዮሐ.7:38 ተመሳሳይ ነገር ነው ያስተማረው። በዚህም ቦታ በእርሱ የሚያምን ከሆዱ ውስጥ የሕይወት ውሃ ወንዝ እንደሚፈልቅ ነበር የተናገረው። እነዚህ "ምንጭ" እና "ወንዝ" የሚሉት ቃላት የማይደርቅና ሳያቋርጥ ሞልቶ የሚፈስ ውሃን ያመለክታሉ። ጌታ ይህን ነገር የተናገረው በእርሱ የሚያምኑ ስለሚቀበሉት ስለ መንፈስ ቅዱስ ነበር።

የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በአንዳንድ አማኞች ሕይወት ውስጥ የማይታይበት ምክንያት እግዚአብሔር እሺ ስለማይል ሳይሆን አማኞቹ እግዚአብሔርን እሺ ስለማይሉ ማለትም በእግዚአብሔር እንደሚገባ ስለማይመላለሱ እንደ ቃሉም ስለማይኖሩ ነው። በአጭር ቃል ስለማይታዘዙ ነው። አንድ ክርስቲያን የማይታዘዝ ማለትም ለእግዚአብሔር ቃል እሺ የማይል ከሆነ ፈቃደኛ አይደለምና መንፈስ ቅዱስ ያንን ሰው አይሞላውም ወይም አይቆጣጠረውም መንፈስ ቅዱስ አስገዳጅ ጌታ አይደለምና።

አንድ አማኝ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሕይወትን በሚኖርበት ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ የራሱ ባህርያት በውስጡ ፈክተው ይታያሉ። ይህ ማለት መንፈስ ቅዱስ አምላክ እንደሆነ ያም ሰው ትንሽ አምላክ ይሆናል ማለት አይደለም። ነገር ግን ያ አማኝ በክርስትና ሕይወት የተለያዩ አቅጣጫዎች ማደጉ ገሃድ ይሆናል ክርስቶስንም መምሰሉ ከፊት ይልቅ ጎልቶ መታየቱ ይቀጥላል።

ክርስቶስን መምሰል እያንዳንዱ ክርስቲያን የተጠራበት ጥሪ ነው። በሮሚ.8:29 ላይ እግዚአብሔር አስቀድሞ የጠራቸው ሁሉ የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ወስኖ እንደሆነ ይናገራል። ጳውሎስ በሌሎችም ቦታዎች አማኞች ክርስቶስን መምሰል እንደሚገባቸው ያስተምራል። (ለምሳሌ 1ቆሮ.11:1፤ ኤፌ.5:1) የክርስቶስን መልክ መምሰል ስጋዊ ወይም አካላዊ መልኩን ሳይሆን ሰው አስቀድሞ ሲፈጠር የታለመለትን የእግዚአብሔር መልክና አምሳል ማለት ነው። እግዚአብሔር "ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር" ሲል ስጋዊ መልክን መናገሩ አልነበረም፤ እግዚአብሔር መንፈስ ነውና። ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሕይወትን ሲኖር እግዚአብሔርን የሚመስል ሰው ይሆናል። ያ ሰው እውነተኛ መንፈሳዊ ሰው ይሆናል።

የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቁ ከጸጋ ስጦታዎች የሚበዙቱ በቤተ ክርስቲያናቸው የሚታይ ምዕመናን ቢሆኑም በአመዛኙ መንፈሳውያን ወይም መንፈስ ቅዱስ የገዛቸው ግን አልነበሩም። ስጋውያን ነበሩ ማለትም ስጋቸው የነገሰባቸውና መንፈሳዊ ብስለትና ዕድገት የጎደላቸው ነበሩ። እንደማያድጉ ሕፃናት ስለሆኑበት ሐዋርያው ጳውሎስ ወተት

ሊግታቸው ተገድዶ ነበር። (ምዕ.3) በመካከላቸው መለያየት ከመኖሩ የተነሳ ሰዎችን እየተከተሉና በቡድን እየተከፋፈሉ እንደ አንድ አካል መሆን የነበረባትን ቤተ ክርስቲያን ይለያዩ ነበር። (ምዕ.1-4) አህዛብ እንኳ የማይሰሩት የዝሙት ተግባር በመካከላቸው ይፈጸምና በዚህም በማዘን ፈንታ ይታበዩ ነበር። (ምዕ.5) እርስ በርሳቸው እየተጣሉና እየተካሰሱ ከመመላለስ አልፈው ለዕርቅም ሆነ ለክርክር ወደ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች በመሄድ ፈንታ ወደ መንግሥት ፍርድ ቤትና ወደ ዓለማውያን ዳኞች እየሄዱ ይሟገቱ ነበር። (ምዕ.6) አንዳንዶቻቸው በመንፈሳዊ ነፃነታቸው እየተመኩ ሌሎችን ያልበሰሉትን ሲያሰናክሉ ደንታቢሶች፥ የሚመኩና የሚታበዩ ለአምላካዊ ስልጣንም የማይገዙ ነበሩ። (ምዕ.8-9) የጌታን ራት ምንነት የማያስተውሉና ሲሰበሰቡም ደንታ የሌላቸው ነበሩ። (ምዕ.10-11) የጸጋ ስጦታዎች ተሰጥተዋቸው ሳለ ሰጪውን በማክበርና ጉባዔውን በማነጽ ፈንታ አንዱን ስጦታ ከሌላው በማስበለጥና ያለገደብ በመለጠጥ (በማሳበጥ) የኔ ይበልጥ በማለት እንቁልልጭ የሚጫወቱ እንዲሁም በአገባብና በስርዓት ሳይሆን በሁከትና በመስለኝ ብቻ በማገልገል የሚተራመሱ ነበሩ። (ምዕ.12 እና 14) ፍቅር እንደጎደላቸው በግልጽ ይታይ ነበር። (ምዕ.13) ትንሳኤ ሙታንን የሚክዱም ሰዎች በመካከላቸው ይኖሩ ነበር። (ምዕ.15) ታዲያ እኒህን መሰል ራሳቸውን ለመንፈስ ቅዱስ ሊያስገዙ ያልፈቀዱ ምዕመናን ያለመገዛታቸው በተግባራቸው እየታየ መንፈስ ቅዱስ ገዝቷቸው ነበር ማለት የሚገባ አይደለም።

## መጽሐፍ ቅዱሳዊው የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ምልክት ምንድነው?

አንዳንዶች የጸጋ ስጦታን የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ምልክት አድርገው ይቀበላሉም ያስተምራሉም። የቆሮንቶስ ምዕመናን ስጦታዎች ነበሯቸው። ወገባቸው የተያዘው ግን ፍሬው ላይ ነው። ስጦታ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ምልክት አይደለም። ይህን አሳብ ላሰምርበት እፈልጋለሁ፤ ስጦታ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ምልክት በፍጹም አይደለም። የስጦታዎችን መልክ በተመለከተ አንዳንዶች የመስከና የአደባባይ ሲመስሉ ሌሎች ደግሞ የማጀት፥ የእልፍኝና የጓዳ ይመስላሉ። ይሁን እንጂ ዓላማቸው አንድ ነው ያም አካልን ማነጽ ሲሆን የዚህ እነጻ ውጤት ደግሞ የጌታ ክብር ነው።

ክርስቲያኖች ሁሉ ስጦታ ወይም ስጦታዎች አሏቸው። ስጦታ የሌለው ክርስቲያን የለም። አንድ ክርስቲያን ግን ስጦታ ኖሮት መንፈስ ቅዱስ የገዛው በመሆን ፈንታ ሥጋዊ ክርስቲያን ሆኖ ሊኖር ይችላል። መንፈሳዊው ክርስቲያን ስጦታውን አገልግሎት ላይ እንደሚያስግራው ስጋዊውም እንዲሁ ሊያደርግ ይችላል። የሚያይ ዐይን ላለው ልዩነቱ ይታያል። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆኑን የቆሮንቶስ ምዕመናን ናቸው። እነርሱም በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቁና ስጦታዎችም በዝተው የተሰጧቸው ቢሆኑም ስጋቸው የሰለጠነባቸው ሰዎች ነበሩ። 'መንፈሳውያን' ሊባሉ ሲገባቸው 'ስጋውያን' ተባሉ። ማደግ ሲጠበቅባቸውና ሲገባቸው እንጭጭና ጮርቃ ሆነው ኖሩ። ለምን ቢባል እኒህ መንፈስ ቅዱስ የሞላቸው ሳይሆኑ ስጋ የነገሠባቸው ነበሩና። አማኞች በውስጣቸው ያለውን ማናቸውንም የጸጋ ስጦታ በተገቢው መንገድ ሊያገለግሉበት የሚችሉት በመንፈስ ቅዱስ እየተሞሉ ሲኖሩ ነው። ያለዚያ መታነጽም አይኖርም፥ ጌታም አይከበርም፥ ስለ ቤተ ክርስቲያንም መልካም ነገር አይሰማም። ለምሳሌ በመንፈስ ቅዱስ የማይገዛ ወይም የማይሞላ የስብከት ስጦታ ያለው ሰው የደኅንነታችን እራስ የሆነውን ክርስቶስን በማሳየት ፈንታ ስጦታውን የሰዎች መደብደቢያ ዱላ ሊያደርገው ይችላል። የፈውስ ስጦታ የተሰጠው ሌላው ደግሞ የፈዋሹን አምላክ ባህርይ በማሳየት ፈንታ መድረኩን በእርሱ በእራስነቱ ሊሞላውና ሊታይበት ይችላል። ሌሎችም ስጦታዎች እንዲሁ ሊበላሹና አካልን ለመገንባት ሳይሆን የአካል አንድ ክፍልን ብቻ ለማሳበጥ ሊውሉ እንደሚችሉም ማየት ይቻላል። የአካል ክፍል ሲያብጥ ደግሞ በራሱ በሽታ ነው። ስጦታዎችን በመንፈስ ቅዱስ መንገድ ሳይሆን በራስ ጉልበትና ጥበብ ተግባራዊ ስናደርግ ፍሬ ቢስ ብቻ ሳይሆን እንዲያውም መራራ ፍሬ የሚያፈራ የስጋ ሥራ እናደርገዋለን።

አንዳንድ አስተማሪዎች ሙላትን 'ዳግመኛ ጥምቀት'፥ 'ዳግመኛ ቡራኬ ወይም ብጽዕና' ወይም 'ዳግመኛ ግብረ-ጸጋ' ይሉታል። እኒህን ቃላት በአዲስ ኪዳን ውስጥ አናገኝም፤ ብንጠቀምባቸውም እንኳ ሙላት የሚለውን ቃል ኃይሉንና ውበቱን ቢቀንሱ እንጂ አይጨምሩበትም። የሚቀንስበትም መንገድ ጥምቀት አንዴ የሚደረግን ክስተት ሲያመለክት ሙላት ደግሞ ያለማቋረጥ የሚደረግን ነገር ሂደት የሚያሳይ በመሆኑ ነው። አንድ ጸሐፊ እንዳለው "በመንፈስ ቅዱስ ስንሞላ ጥያቄው ምን ያህል እርሱ በኛ ውስጥ መኖሩ አይደለም፤ ሥራው መጠናዊ አይደለምና። እኛ ምን ያህል መንፈስ እንዳለን ሳይሆን እኛ ለመንፈስ ቅዱስ ምን ያህል እንደተሰጠነው ነው መሆን ያለበት።"[8] መንፈስ ቅዱስ ምን ያህል እኛ እንዳለነው ስንል ምን ያህል እርሱ የሕይወታችን ሁሉ ክፍል ተቆጣጣሪ ነው እንደማለት ነው። እርሱ የአስተሳሰባችን፥ የንግግራችን፥ የድርጊታችን፥ የግንኙነቶቻችን፥ የአገልግሎታችን ሁሉ ተቆጣጣሪያችንና መሪያችን ሊሆን ይፈልጋል። በሌላ ቋንቋ ለእርሱ ፍላጎት

ምን ያህል የተሰጠንና የምንሰማው የምንታዘዘውም ነን እንደማለትም ነው። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ከኛ ውጪ የሆነ ኃይል መጥቶ እኛነታችንን ሲወርረን ማለት አይደለም። ይህንንም አሳብ እንደገና ላደምቀው እወዳለሁ፤ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ማለት ከኛ ውጪ የሆነ ልዩና የማናውቀው መንፈስ መጥቶ እኛን ሲወርረን ማለት አይደለም። ነገር ግን ስናምን በኛ ውስጥ መኖር የጀመረው መንፈስ ቅዱስ እኛነታችንን ሲቆጣጠረው ማለት ነው። አንዳንድ ሰዎች ሙላትን ከውጪያቸው ወደ ውስጣቸው እንደሚገባ ተጽዕኖ ወይም ኃይል በመውሰድ ለስሜታዊ ግለትና ሰብዓዊ ብቻ ለሆነ የስህተት አሰራር ይጋለጣሉ። ከውጪ የሚጠበቅ ከሆነ ደግሞ መንፈሳዊ ብቻ ሳይሆን አካላዊ የሆነ ነገርም እንዲደረግ መጠበቁ የማይቀር ነው፤ ብዙዎችም ያደርጉታል። ከዚህ የተነሳ መውደቅና መንፈራፈር፥ መንቀጥቀጥና መጮፈር መታየቱ የተለመደ ነው። እንዲህ የሚሆኑት ሰዎች ከዚህ በፊት በውስጣቸው ከነበረው የተለየና የበለጠ መንፈስ ያገኙ መስሎ ይሰማቸዋል። ይህን ዓይነት ነገር የሚያደርጉና የሚያስደርጉ ምዕመናንና አገልጋዮች ደግሞ ከዚህ በፊት ከሰሙትና ካዩት የበለጠ ነገር ሲደረግ የማየት ረሃብና ጥማት ያድርባቸዋል። መጀመሪያ አንድ ሰው ሲወድቅ ካዩ፥ በሚቀጥለው ሲዘል ማየት ይመኛሉ፥ ሲዘል ካዩ ደግሞ በሚቀጥለው ከጣራ በላይ እንጣጥ ሲል ማየት ይናፍቃሉ። ከላይ እንደተጠቀሰው ሙላት ስንል እኛ የመንፈስን ብዛት ሳይሆን መንፈስ የኛን ሁለንተና የገዛበትን መጠን ነው ማሰብ ያለብን። መንፈስ ቅዱስ በብዛት ሰፍረን የምንወስደው ወይም ተሰፍሮ የሚሰጠን ሲሰጠንም ከእርሱ የሆነ ክፍል የሚቀነስበት የሆነ ነገር አይደለም።

መንፈስ ቅዱስ እኛ ካመንን በኋላ በነገራችን ሁሉ ውስጥ እየገባ የጉዞ አቅጣጫችንን እየቀየሰ ሊመራን የሚወድ አምላክ ነው። ሲመራንና ስንታዘዘው ለምናደርገው ነገር የምናደርግበትን ኃይልና ድፍረት ይሰጠናል ውጤቱም የምዕመናን መታነጽና የጌታ ክብር ይሆናል። ደግሞም የመንፈስ ቅዱስ ዓቢይ ተግባር ጌታ ኢየሱስን ማክበርና እንዲከበር ማድረግ ነው ሌላው ቀርቶ ራሱን እንኳ አያሳይም ማለትም በምንም ሌላ ነገር ወልድ እንዳይታይና እንዳይከብር ምንም ጭጋግን አይፈጥርም። (ዮሐ.16:14) ዛሬ በአንዳንድ ጉባኤዎች መንፈስ ቅዱስን ለማክበር ተብሎ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑም ልምምዶች ይጋበዛሉ። መንፈስ ቅዱስ እንዲመጣ የአክብሮት ጥሪ ይደረጋል፤ እርሱ የከበረ ለማስመሰልም የሆኑ ሰው ሰራሽ ነገሮች ያደርጋሉ። የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ግን ኃጢአታችንን ወስዶ የሞተልንን ዛሬም በአብ ቀኝ በክብር ያለውን ጌታ ማክበርና እኛም እንድናከብረው ማድረግ ነው።

አዲስ ኪዳን ሙላትን ሳያቋርጥ እንደሚኖር ሂደት አድርጎ እንደሚያቀርበው ሁሉ (ለምሳሌ በርናባስ ሐዋ.11:24) ለአንድ የተለየ ዓላማ እንደሚፈጸም ውሱን ድርጊትም አድርጎ ያቀርበዋል። በርናባስን መንፈስ

ቅዱስ የሞላበት አድርጎ ሲያቀርበው በዚህ ክፍል በነዋሪ ሁኔታ ባለማቋረጥ ለመንፈስ ቅዱስ የተሰጠ ሰው መሆኑን መናገሩ ሲሆን፥ በሌላ በኩል ደግሞ መንፈስ ቅዱስ አንድ የተለየ ነገርን ለማድረግ መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ሲሞላ እናያለን። ለምሳሌ ዘካርያስ ትንቢት የተናገረበትን (ሉቃ.1) ወይም ሐዋርያትና ደቀ መዛሙርት በድፍረት ቃሉን የተናገሩበትን (ሐዋ.4) ቦታዎች ስናይ ለአንድ የተለየ ዓላማ መሞላታቸውን በግልጽና በማያሻማ ሁኔታ እናነባለን።

በዘመናችንም መንፈስ ቅዱስ የተለወጠ ስራን አይደለም እየሰራ ያለው። ለአገልግሎት ይሞላል፥ በአማኞችም በሙላት ይኖራል። ነገር ግን መሰጠትን ይጠይቃል። ለተወሰነ ወይም ልዩ አገልግሎት መሞላትም የተለየ የመንፈስ መጠንን መቀበል ሳይሆን ለመንፈስ ቅዱስ ሥራና ምሪት አልፎ ለመሰጠት ፈጽሞ መፍቀድ ማለት ነው። አገልግሎቱ በተከናወነ ጊዜም ጌታ ይከብራል። በሐዋ.4:31 ይህን ነው የምናገኘው። መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ላይ በአንድ ወቅት ለአንድ የራሱ አሰራር ሊወርድባቸው ማለትም ሁለንተናቸውን አካላዊ በሆነ መንገድ እንዲሰማቸውም በማድረግ ሊቆጣጠራቸው ይችላል። ጥቂት ላብራራው፤ ለምሳሌ አንድ ሰው በስደት ውስጥ ወይም በሰማዕትነት ሲያልፍ ወይም በአገልግሎቱ ወቅት ፍርሃትና መሰል ስሜቶች ቢሰሙት መንፈስ ቅዱስ በሚያበረታና ኃይልን፥ ጥበብን፥ ቃልን፥ ድፍረትን፥ መልስን ወዘተ. በመስጠት በውስጡና አብሮትም መሆኑን ሊመሰክርለት ይችላል። ሙላት የማያቋርጥ ለእግዚአብሔር የመሰጠት ሕይወት ነው።

የራሱ ገንዘብ በሆኑት ሰዎቹ ላይ እግዚአብሔር በሰው ኃይልና ብርታት ሊከናወኑ ቀርቶ የማይሞከሩ አስደናቂ ነገሮችን መስራት ይችላል። በዘካ.4:6 ላይ ከዘካርያስ ጋር ይነጋገር የነበረው መልአክ "በመንፈሴ እንጂ በኃይልና በብርታት አይደለም ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር" አለው። ከበፊቱ ባሉት ጥቅሶች (ዘካ.4:1-3) ዘካርያስ የሚያስገርም ነገር ነበር ያየው። ሰባት መብራቶች የነበሩበት ሁለንተናው ወርቅ የሆነ መቅረዝ አየ። ይህ መቅረዝ በራሱ ላይ የዘይት ማሰሮ ሲኖረው በቀኝና በግራው ደግሞ ሁለት የወይራ ዛፎች አሉ። መቅረዙ እንዲበራ ዘይት ያሻዋል፤ ዘይቱም ደግሞ በማሰሮ አለ፥ በቧንቧም ሆኖ ወደ መቅረዙ እየፈሰሰ ያለማቋረጥ እንዲበራ ያደርገዋል። በማሰሮው ያለው ዘይት የሚያልቅ እንኳ ቢሆን በግራና ቀኝ ያሉቱ የወይራ ዛፎች ሳይጠፋ ይበራ ዘንድ እንደማያቋርጥ ምንጭ ዋስትናው ናቸው። መቅረዙ ሳያቋርጥ እንዲበራ ዘይቱን ያለማቋረጥ መሞላት እንዳለበት ክርስቲያንም እውነተኛ የዓለም ብርሃን ለመሆን ሳያቋርጥ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ መሆን ይገባዋል።

መንፈስ ቅዱስ አምላክና የሥላሴ አካል ቢሆንም የእርሱ ቀዳማይ ተግባር ኢየሱስን መመስከርና ማክበር ነው። እርሱ ስለ ጌታ ይመሰክራል (ዮሐ.15:26)

ጌታንም ያከብራል። (ዮሐ.16:14) አንድን ሰው መንፈስ ቅዱስ ሞላበት ስንል እነዚህን መስፈርቶች መጠቀም አለብን።

- ሕይወቱ ወይም ሁለንተናው በሙላት ጌታን ይመሰክራል?
- ይህስ ሰው ጌታን ይፈራል? ያከብራል?
- ሰዎችስ በዚያ ሰው ሕይወት ውስጥ ክርስቶስን ያስተውላሉ?

መንፈስ ቅዱስ የሰዎች መከበሪያ ወይም ሰዎች ትኩረትን ወደ ራሳቸው የሚስቡበት መሳሪያ አይደለም። መንፈስ ቅዱስ ሌላው ቀርቶ እራሱን እንኳ የሚያጎላና ክብርን ለራሱ የሚወስድ አይደለም ክርስቶስን እንጂ። አንዳንድ ክርስቲያኖች በሚያሳዝን መንገድ እራሳቸውን የአገልግሎታቸው ማዕከል ያደርጉታል።

መንፈስ ቅዱስ እርሱ አምላክ ነውና እርሱ የሞላበት ሰው ከቅድስና ወደ ጎላና ወደ ደመቀ ቅድስና እየተሸጋገረ የተለየ ሕይወትን ይኖራል። መቀደስ ማለት መለየት ማለት ነው። ይህም ከኃጢአት ኃይልና ለኃጢአት ከመገዛት የመለየትን እንጂ የገዳም ኑሮን የሚያመለክት አይደለም። መንፈስ የገዛው ሰው ከኃጢአት የተለየ ኑሮን መኖሩ በጌታም በሰዎችም ፊት የተገለጠ ይሆናል። እግዚአብሔር በእርሱ መኖሩ የተመሰከረለት የብሉይ ኪዳኑ ዮሴፍ እንዲህ ባለ ቅድስና የሚመላለስ ነበር። የአሳዳሪው ሚስት አብሯት እንዲተኛ መላልሳ ባጠየቀችው ጊዜ የሰጣት መልስ "በእግዚአብሔር ፊት እንዴት?" የሚል ዓይነት ነበር። በመንፈስ ቅዱስ የተገዛ ሰው በአምላክ ዓይኖች ፊት እየተመላለሰ ያለ መሆኑ እጅግ ጎልቶ የሚሰማው ሰው ነው።

ክርስቲያኖች ያለ ቅድስና ሲመላለሱ የእግዚአብሔር ስም እንደሚሰደብ ክርስትናም እንደሚንቋሸሽ ያህል አማኞች በቅድስና በሚመላለሱበት ጊዜ ደግሞ እግዚአብሔር ይከብራል። ሰው በራሱ ኃይል በቅድስና መኖር አይችልም። በቅድስና መኖር የሚቻለው ቅዱስ የሆነው ይህ አምላክ በአማኙ ውስጥ ሲሆን ሲመራውና ሲሞላው ነው። የፊቱ ብርሃን በኛ የኛ ብርሃን ደግሞ በዓለም ሲበራ ሰዎች ጌታን ያከብሩታል። እንደ እውነቱ ከሆነ ክርስትና ፈጽሞ ሊኖሩት የማይቻል ሕይወት ነው፤ ከብሉይ ኪዳን ህግጋትም የባሰ እጅግ ጠንካራ ነው። (ማቴ.5-7) በክርስትና ሊኖር የሚቻለው ግን ይህ መንፈስ በዚያ አማኝ ውስጥ ሆኖ የራሱን ኑሮ ሲኖር ነው።

ስለዚህም ሙላት ለአገልግሎት አስፈላጊነቱ የማያጠያይቅ ነገር ነው። ክርስቲያን የሚያገለግለው አገልግሎት መንፈሳዊ እንደመሆኑ በስጋ ጉልበት ወይም በአዕምሮ ጠቢብነት ብቻ የሚከናወን አይደለም። መንፈስ ቅዱስ ያንን አገልጋይ ማጎልበት ያንንም አገልግሎት መባረክ ይወዳል። ጴጥሮስ በሐዋ.2 የሰበከውን ስብከት ከመስበኩ በፊት በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ነበር። በሐዋ.4:8 እንደገና በባለሥልጣኖች ፊት በተናገረ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ነበር። ከዚህም በኋላ ተፈትተው እርሱና ዮሐንስ ወደ ደቀ መዛሙርት መጥተው ጸለዩና አሁንም መንፈስ ቅዱስ ሞልቶባቸው ቃሉን በግልጥ ተናገሩ። መንፈሳዊ አገልግሎት ከመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ሙላት የተለየ ከሆነ ፍሬቢስ ነው። የእግዚአብሔር ስራ በእግዚአብሔር መንገድና በእግዚአብሔር ኃይል ከተደረገ ግን ቤተ ክርስቲያን ትባረካለች እግዚአብሔርም ይከብራል።

የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ለስብከት ወይም መሳይ የመድረክ አገልግሎት ብቻ ሳይሆን ለሁሉም የአገልግሎት ዘርፍ ግድና አስፈላጊ ነገር ነው። በሐዋ.6 ለምናገኛቸው በማዕድ እንዲያገለግሉ ለተመረጡት ዲያቆናት እንኳ እንደ መመዘኛ ከተዘረዘሩት ነጥቦች አንዱ በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ መሆናቸው ነው። (ሐዋ.6:5) ቀድሞም ሆነ ዛሬ በብዙዎች አብያተ ክርስቲያናት የሚታዩት ጉልህ ችግሮች ምንጭ መንፈስ ቅዱስ ያልሰለጠነባቸው ሰዎች በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ መሰልጠናቸው ነው። በብሉይ ኪዳን በዘጸ.35 የምናገኛቸው ባስልኤልና ሌሎቹም ጠቢባን የእግዚአብሔርን መቅደስ ዕቃዎች ሲሰሩ የእግዚአብሔር መንፈስ የሞላባቸው ነበሩ። እነዚህ ሰዎች የሚሰሩት ስራ ከሰዎች ጋር የተያያዘ ሳይሆን ከዕቃዎች ጋር የተያያዘ ነው። ዕቃ ለመስራት በመንፈስ ቅዱስ መደገፍ ካስፈለገ ከሰው ጋር የተቆራኘ አገልግሎት ለማገልገልማ ምን ያህል የእርሱ ኃይል እንደሚያሻ ግልጽ ነው። ለአዲስ ኪዳን አማኞች ወይም አገልጋዮች በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት አስፈላጊነት የምርጫ ጉዳይ ያልሆነ እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው። እንዲያውም ትዕዛዝ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ለጥቂት 'አገልጋዮች' ለሚባሉቱ ወይም ይህ መጠሪያ በዘልማድ ለተሰጣቸው ብቻ የታደለ አይደለም። እንደ አዲስ ኪዳን እውነት ከሆነ ዳግም የተወለዱ አማኞች ሁሉ አገልጋዮች ናቸው ስለዚህ አማኝ ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሕይወትን እንዲኖር ይጠበቅበታል። ሙላት የዕለት ተዕለት የአማኝ የሕይወት ስርዓትና የመታዘዝና የመገዛት ውጤት የሆነ የተትረፈረፈ ሕይወትና ፍሬያማ አገልግሎት ምንጭ እንጂ ልዩና እንግዳ አድራጎት አይደለም።

## የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በአዲስ ኪዳን

የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተጻፈባቸው ቦታዎች ብዙ አይደሉም። በአስራ አራት ቦታዎች ብቻ መንፈስ ቅዱስና ሙላት ተያይዘው እናገኛለን። እነዚህን ቦታዎች ማየቱና ሙላትን ተከትለው ምን ድርጊቶች እንደተፈጸሙ ደግሞም በምን ያህሉቹ ውስጥ ልሳን እንዳለም በእግረ መንገድ መመርመሩ ጥሩ ይሆናል።

1. ሉቃ.1:15፤ "ገናም በእናቱ ማህፀን ሳለ መንፈስ ቅዱስ ይሞላበታል።" ይህ በቤተ መቅደስ ውስጥ የጌታ መልአክ ለዘካርያስ የተናገረው ቃል ነው። መቼ ስለመፈጸሙ እርግጠኛ አልሆንም። ምናልባት ማርያም ኤልሳቤጥን በጎበኘቻትና በኤልሳቤጥ በራሷ መንፈስ ቅዱስ በሞላባት ጊዜ ተፈጽሞ ይሆናል። ይህ ሙላት መጥምቁ ዮሐንስ ገና ከማህፀን ጀምሮ ለጌታ ሥራ መለየቱን ያመለክታል።

2. ሉቃ.1:41፤ በዚህ ክፍል የምናያት ሴት የመጥምቁ ዮሐንስ እናት ኤልሳቤጥ ናት። "ኤልሳቤጥም የማርያምን ሰላምታ በሰማች ጊዜ ፅንሱ በማኅፀንዋ ውስጥ ዘለለ በኤልሳቤጥም መንፈስ ቅዱስ ሞላባት በታላቅ ድምጽም ጮኽ እንዲህ አለች..." በዚህና በሚቀጥሉት ሁለት ጥቅሶች የምናያቸው ነገሮች አብ እንደሰጠው ተስፋና ጌታም እንደተናገረው መንፈስ ቅዱስ በበዓለ ኀምሳ ቀን ከመውረዱ በፊት የሆኑ ነገሮች ናቸው። ኤልሳቤጥ በመንፈስ ቅዱስ እንደተሞላች በታላቅ ድምጽ ጮኽ ነበር፥ የልዑል እግዚአብሔርንም ድንቅ ሥራ ገልጣ ተናግራ ነበር። መንፈስ ቅዱስ ሕይወትን ሲሞላ ድምጽ አውጥቶ መጮህና ገልጦ መናገርም አለ። ይህን የመሰለ ነገር በጉባዔ ውስጥ ቢከሰት ተናጋሪውን መመርመርና ማወቅ ተገቢ ቢሆንም ነገሩን ስሜታዊ ብቻ አድርጎ በደፈናው ማውገዝ ግን ትክክል አይደለም።

3. ሉቃ.1:67፤ በዚህ ክፍል የምናየው ደግሞ የኤልሳቤጥ ባልና የዮሐንስ አባት ዘካርያስ ነው። "አባቱ ዘካርያስም መንፈስ ቅዱስ ሞላበትና ትንቢት ተናገረ እንዲህም አለ..." እዚህ ክፍል ውስጥ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ከሞላበት በኋላ ካህኑ ዘካርያስ የሚያስደንቅን ትንቢት ስለ ሕፃኑ ዮሐንስ እና ስለ መሲሁም ጭምር ሲናገር እናያለን።

4. ሉቃ.4:1፤ በዚህ ክፍል የምናነበው ደግሞ ከሌሎቹ የተለየ ነገር ነው። ልዩ የሚያደርገውም በዚህ ክፍል በመንፈስ ቅዱስ የተሞላው ኢየሱስ ራሱ መሆኑ ነው። "ኢየሱስም መንፈስ ቅዱስ መልቶበት ከዮርዳኖስ ተመለሰ በመንፈስም ወደ ምድረ በዳ ተመርቶ አርባ ቀን ከዲያብሎስ ተፈተነ" ይለናል። ጌታ ምንም እንኳ ባልተጓደለ መለኮታዊ ክብር ቢኖርም ሥጋ በመልበሱ ለእኛም ምሳሌ ይሆነን ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ ሲደገፍ ፈተናንም

ሲጋፈጥና ሲያሸንፍ እናገኘዋለን።

5. ሐዋ.2:4፤ በዚህ ክፍል ያለው ቃል እንዲህ ይላል፤ "በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር" ይህ ዕለት መንፈስ ቅዱስ የወረደበት ቤተ ክርስቲያንም የተወለደችበት ዕለት ነው። ይህ መጥምቁ ዮሐንስ እና ራሱም ጌታችን ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የተናገሩት የተፈጸመበት ዕለት ነው (ሉቃ.3:16፥ ሉቃ.24:49፥ ሐዋ.1:8) በተጨማሪም ስለ መንፈስ መፍሰስ በኢዩ.2:28-29 የተነገረው ትንቢት ከፊል ፍጻሜም ነው። ይህ ከሆነ በኋላ እነዚህ ወደ መቶ ሃያ የሚያህሉ ደቀ መዛሙርት በሌሎች ቋንቋዎች እንደተናገሩ ተጽፏል። እነዚህ ልሳናት በእርግጥ የሚታወቁ በርካታ ቋንቋዎች ነበሩ።

6. ሐዋ.4:8፤ "በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ መንፈስ ቅዱስን ተሞልቶ እንዲህ አላቸው..." ይህ በዚህ ቦታ የተፈጸመው ነገር በሐዋ.3 አንድ ሽባ ሰው በጌታ ስም ከተፈወሰ በኋላ የካህናት አለቆች፥ ሰዱቃውያንና የመቅደስ አዛዥ ሌሎችም ሆነው አስረው ሊመረምሩአቸው በታሰሩ ማግስት ወደ ፊታቸው ባቀረቧቸው ጊዜ የሆነ እውነት ነው። ጴጥሮስ ቀደም ሲል ባየነው ክፍል ከሌሎቹ ሐዋርያትና ደቀ መዛሙርት ጋር በመንፈስ ቅዱስ መሞላቱ በግልጽ ተጽፏል፤ በዕለቱ የሰበከውም እርሱ ነበር። እዚህም በድጋሚ ሲሞላ ነው የምናየው። የመሞላቱ ውጤትም በድፍረት በአለቆች ፊት ቃሉን በሙላትና በፍጹም ግልጥነት መናገሩ ነው።

7. ሐዋ.4:31፤ እነጴጥሮስ ተፈትተው ወደ ወገኖቻቸው ከመጡና የሆነውንና ያሏቸውን ነገር ሁሉ ከዘገቡ በኋላ በአንድነት ጸሎት ጸለዩ። "ከጸለዩም በኋላ ተሰብስበው የነበሩበት ሥፍራ ተናወጠ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው የእግዚአብሔርንም ቃል በግልጥ ተናገሩ።" በዚህ ሥፍራ የሆነው ልዩ ክስተት የተሰበሰቡበት ሥፍራ መናወጥ ሲሆን የተሞሉት ሁሉም ናቸው ከተሞሉ በኋላ የሆነው ደግሞ ቃሉን በግልጥ መናገራቸው ነው።

8. ሐዋ.6:3-5 ሐዋርያት በጸሎትና ቃሉን በማገልገል እንዲተጉ ብለው ዲያቆናት እንዲመረጡ ለቤተ ክርስቲያን ጉዳዩን አቀረቡ። እንዲመረጡም የታሰቡትን መመዘኛ ሲነግሯቸው "ወንድሞች ሆይ በመልካም የተመሰከረላቸውን መንፈስ ቅዱስና ጥበብም የሞላባቸውን ሰዎች ከእናንተ ምረጡ...አሏቸው። ይህም ቃል ሕዝቡን ሁሉ ደስ አሰኛቸው፤ እምነትና መንፈስ ቅዱስ የሞላበትን ሰው... መረጡ።" አገልጋዮችን ለመምረጥ ከቀረቡት መመዘኛዎች አንዱ በመንፈስ ቅዱስ መሞላታቸው ነው። እነዚህ ሰዎች ከመመረጣቸው አስቀድመው መንፈስ ቅዱስ የሞላባቸው መሆናቸው የተመሰከረለት ጉዳይ ነው። በኋላ ግን ሐዋርያት ጸለዩላቸው እጃቸውንም

ሜኑባቸው። ይህ እጅ መጫን መሾም ነው።

9. ሐዋ.7:55፤ ይህ ክፍል ስለ ሰማዕቱ እስጢፋኖስ እንዲህ በማለት ይናገራል፥ "መንፈስ ቅዱስንም ተሞልቶ ወደ ሰማይ ትኩር ብሎ ሲመለከት የእግዚአብሔርን ክብር ኢየሱስንም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አየና..." እስጢፋኖስ ይህን መከራ ሊቀበል ያስቻለው መንፈስ ቅዱስ ነው። በሌላም ቦታዎች በመከራ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ሕይወት ከሚሰራው ድርጊት አንጻር ሲታይ ይህ አሰራር እውነት ነው።

10. ሐዋ.9:17፤ ይህ ደግሞ ሐናንያ አሳዳጅ የነበረውን ሳውልን መጀመሪያ ባገኘበት ጊዜ የሆነው ትዕይንት ነው። "ሐናንያም ሄዶ ወደ ቤቱ ገባ እጁንም ጭኖበት ወንድሜ ሳውል ሆይ ጌታ እርሱም በመጣህበት መንገድ የታየህ ኢየሱስ ነው ደግሞ ታይ ዘንድና መንፈስ ቅዱስ ይሞላብህ ዘንድ ላከኝ አለ።" በዚህ ክፍል ሳውል መንፈስ ቅዱስ የተሞላበትን ሁኔታና የተከተለውን ነገር በዝርዝር አናገኝም፤ ይሁን እንጂ ሐናንያ የተላከውን ተልዕኮ መፈጸሙን ሳውልም በመንፈስ ቅዱስ መሞላቱን እናምናለን።

11. ሐዋ.11:24 "ደግ ሰውና መንፈስ ቅዱስ እምነትም የሞላበት ነበረና።" ይህ ቃል ስለ በርናባስ የተነገረ ነው። ከዚህ ቃል እንደምንረዳው ቅጽበታዊ የሆነን ነገር ወይም በዚያን ጊዜ በርናባስ በመንፈስ ቅዱስ ሲሞላ አይደለም የምናየው ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ሞልቶበት የሚኖርበት መኖሪያው አድርጎት የተደላደለበት መሆኑን የሚያሳይ አሳብ ነው።

12. ሐዋ.13:9፤ "ጳውሎስ የተባለው ሳውል ግን መንፈስ ቅዱስን ተሞልቶ ትኩር ብሎ ሲመለከተው..." በሐዋ.9:17 እንደተረዳነው ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቷል። ከሆነ ይህ ዳግመኛ የተገለጸ መሆኑ ነው። ሙላት የአንድ ጊዜ ክስተት ብቻ ያለመሆኑን ከዚህም ከሐዋ.4:8 እና 31ም እናገኛለን። በዚህ ቦታ የምናነብበው ጳውሎስ ኤልማስ የተባለውን ጠንቋይ ሲገስጸውና ይህም ሰው እስከጊዜው ድረስ ዕውር ሲሆን ነው።

13. ሐዋ.13:52፤ በዚህ ክፍል ያለው ቃል "በደቀ መዛሙርትም ደስታና <u>መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው</u>" ይላል። ይህ ክፍል እንደሚያስረዳን ይህ መሞላት የጲስድያ በሆነችው አንጾኪያ ከሆነ ድንቅ የወንጌል ሥርጭትና ከዚህም ጋር ከተያያዘ ስደትን ከተከተለ ደስታ ጋር ተያይዟል።

14. ኤፌ.5:18፤ "መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ ይህ ማባከን ነውና" ይህ ትዕዛዝ ነው። የኤፌሶን ምዕመናን የታዘዙት ትዕዛዝ ዛሬም አማኞች ሁሉ ሊከተሉት የሚገባ ትዕዛዝ ነው። በመንፈስ ቅዱስ መሞላትና በወይን ጠጅ መስከር በመመሳሰል ሳይሆን በመነጻጸር ነው ጎን

ለጎን የተጠቀሱት። ኤፌ.5:19-21 ከላይኛው ጥቅስ ተለይተው መታየት የሌለባቸው አሳቦች ናቸው። መዝሙር፥ ዝማሬ፥ መንፈሳዊ ቅኔ መቀኘትና መዘመር እንዲሁም ሁልጊዜና ስለ ሁሉ በጌታ ስም እግዚአብሔርን ማመስገንና በክርስቶስ ፍርሃት አንዱ ለሌላው መገዛት በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት ውጤቶች ናቸው። ለዚህም ነው እነዚህ አሳቦች ከላይኛው አሳብ ጋር ተያይዘው የተገለጹት። ይህ ክፍል ደግሞ ልመና ወይም አስተያየት ሳይሆን ትዕዛዝ ነው።

እንግዲህ መንፈስ ቅዱስና ሙላት የተያያዙባቸውና የተጠቀሱባቸው ቦታዎች እነዚህና እነዚህም ብቻ ናቸው። ሙላት የአንድ ጊዜ ብቻ ልምምድ ሳይሆን የሁልጊዜ በፈቃድ ለመንፈስ ቅዱስ መገዛት ነው። ሁልጊዜ ሲባል መሞላት እንዳለ መጉደልም አለ ማለት ነው። መጉደል ስላለም ነው መሞላት ያስፈለገበት ምክንያት። መጉደል ሲባልም መንፈስ ቅዱስ አይደለም የሚጎድለው። ጎዶሎዎች የምንሆነው እኛ ነን። ይህም ማለት ሁለንተናችን ለእርሱ ከመሰጠት ውስጥ ሲወጣና እንደ ፈቃዱ ሳይሆን እንደ ፈቃዳችን ስንሄድ ማለት ነው። ለመንፈስ ቅዱስ ምቹ መሆን፥ በመንፈስ ቅዱስ በመሞላት በእርሱ ቁጥጥር ሥር መሆን ከሆነ መጉደል ደግሞ በእርሱ ቁጥጥር ሥር አለመሆን ነው። ክርስቲያኖች በመንፈስ የተገዙና በእርሱ ቁጥጥር ሥር የሚሆኑ እንደሚሆኑ ሁሉ ለእርሱ የማይታዘዙና ራሳቸውን በራሳቸው የሚመሩ የሚሆኑበት ጊዜም ይኖራል። ክርስቲያን በውስጡ ላለው ለመንፈስ ቅዱስ የሚታዘዝና በእርሱም የሚመራ ሲሆን መንፈሳዊ ክርስቲያን እንደሚሆን ሁሉ እራሱን በራሱ እየመራና ስጋዊ ክርስቲያን እየሆነ መኖር ደግሞ ይችላል። ለዚህ ነው ክርስትና ያልተቋረጠ የአማኝና የጌታ ግንኙነት ነው፥ በየቅጽበቱም በመንፈስ ቅዱስ ተደግፈው የሚኖሩት ኑሮ ነው የሚባለው። በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ማለት ይህ ያልተቆጠበ መሰጠት፥ ለመንፈስ ቅዱስ ምቹ መሆን፥ ያልተቋረጠ ግንኙነትና ያላሰለሰ መደገፍ ነው። ክርስትና ፍጹም መሆን ባይሆንም ከዚህ ያነሰ የክርስትና ሕይወት እንድንኖር ጌታ አላዘጋጀልንም፤ ነገር ግን እኛ ካለመታዘዛችንና ለመንፈስ ቅዱስ ካለመሰጠታችን የተነሳ ነው የተሸነፈ ሕይወት የምንኖረው።

## በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚፈጸሙ ኃጢአቶች

በአዲስ ኪዳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ላይ ሊያደርጉ የሚችሏቸውን ስድስት ያህል ኃጢአቶችን እናገኛለን። እነዚህም መዋሸትና መፈተን፥ መቃወም፥ ማክፋፋት መስደብ፥ ማሳዘን፥ ማጥፋት ናቸው።

## 1. መንፈስ ቅዱስን መስደብ

## (ማቴ.12:22-32፤ ማር.3:20-29)

ይህ ኃጢአት ይቅር የማይባል ኃጢአት ነው። የምንባቡ ክፍል እንደሚያስረዳን ጋኔን ያደረበትን ዕውርና ዲዳ ወደ ኢየሱስ ካመጡ በኋላ ሰውየው እስኪያይና እስኪናገር ተፈወሰ። አንዳንዶቹ ተገርመው መሲሁ እንደሆነ ጠየቁ ሌሎቹ ግን በአጋንንት አለቃ አጋንንትን እንደሚያወጣ ተናገሩ። ጌታም አጋንንትን ያወጣው በእግዚአብሔር መንፈስ መሆኑን ተናግሮ ስድብና ኃጢአት ሁሉ ለሰው ልጆች እንደሚሰረይላቸው መንፈስ ቅዱስን ለሰደበ ግን እንደማይሰረይለት ተናገረ። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ትንተና ከሆነ መንፈስ ቅዱስን መስደባቸው እነዚህ ሰዎች ክርስቶስን ያለመቀበላቸውና ባለመቀበልም መጽናታቸው ነው። ይቅር የማይባል ኃጢአት ደኅንነትን የመርገጥ ኃጢአት ነው። የክርስቶስን ማንነት ማለትም አምላክነቱን የሚገልጠውን በመንፈስ ቅዱስ የተሰራ ስራ ለሰይጣን መስጠት ክርስቶስን ያለመቀበል ነው። የዳኑ ሰዎች የዳኑበትንና በውስጣቸው የሚኖረውን መንፈስ ቅዱስን አይሰድቡም። ክርስቶስን ተቀብለውታልና። የማያምኑ ሰዎች ደግሞ መንፈስ ቅዱስን መስደባቸውን አያውቁም አይቀበሉትምም። አንድ ሰው ክርስቶስን ተቀብሎ የሚድነውና ዳግም የሚወለደው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ነውና መንፈስ ቅዱስን ከሰደበ ወይም ካልተቀበለ ደኅንነትን ሊያገኝ ከቶ አይችልም። ደኅንነትን ካላገኘ ደግሞ በኃጢአቱ ይሞታልና ጠፊ ነው። ይህ መንፈስ ቅዱስን መስደብ የሚባለው ኃጢአት እንግዲህ ክርስቲያኖችን ሳይሆን ያልዳኑትንና ክርስቶስን እንደ ክርስቶስነቱ ሊቀበሉ የማይሹትን የሚመለከት ነው።

## 2. መንፈስ ቅዱስን መቃወም (ሐዋ.7:51)

ይህንን ያላመኑ ሰዎች የሚያደርጉት ኃጢአት ነው። ቃሉን በሐዋ.7:51 እናገኘዋለን እንዲህ ይላል፤ "እናንተ አንገተ ደንዳኖች ልባችሁና ጆሮአችሁም ያልተገረዘ እናንተ ሁልጊዜ መንፈስ ቅዱስን ትቃወማላችሁ አባቶቻችሁ እንደተቃወሙት እናንተ ደግሞ።" ይህ ሰማዕቱ እስጢፋኖስ በከሳሾቹ ፊት የተናገረው ነበር። ይህን ከተናገረም በኋላ ከሳሾቹ ቀድሞም ጌታን የሚጠሉ ነበሩና በቁጣ ወግረው ገደሉት። እስጢፋኖስ የተያዘበት ሥፍራ ምኩራብ ሲሆን የያዙት ይከራከሩት የነበሩት በኋላም የተቃወሙት በሃሰትም የከሰሱት በአይሁድ እምነት ቅንዐት የተዋጡና ክርስቶስን ያላመኑ ስለ እርሱም የተሰጣቸው ምስክርነት ያስቆጣቸው ሰዎች ናቸው። እኒህ መንፈስ ቅዱስን ያላመኑና የማያምኑ ሰዎች ናቸው። እስጢፋኖስ እኒህን ከቀደሙት

እግዚአብሔርንና የእግዚአብሔርን መልዕክተኞች ከተቃወሙና ካሳደዱ አይሁድ ጋር ያመሳስላቸዋል። ከውጪ ሲታዩ የአምልኮ መልክ ያላቸው እነዚህ አይሁድ እውነቱንና የጌታን ጌትነት የማይቀበሉ እንዲያውም አልፈው የሚቃወሙ ናቸው። መቃወም ያለመቀበል ነው። እንግዲህ ይህ መንፈስ ቅዱስን መቃወም እንደ መሳደብ ያላመኑትን የሚመለከት ኃጢአት ነው።

## 3. መንፈስ ቅዱስን ማታለል፥ መዋሸትና መፈታተን (ሐዋ.5:3-9)

በዚህ ክፍል የምናነበው ከአማኞች መካከል የነበሩት ሐናንያና ሚስቱ ሰጲራ የፈጸሙትን ኃጢአት ነው። ኃጢአታቸው ገንዘቡን ማስቀረታቸው አይደለም፤ መሸጥና ያለመሸጥ ከሸጡም በኋላ የወደዱትን ያህል መስጠትና የፈለጉትን ያህል ማስቀረት መብታቸው ነበር። ኃጢአታቸው መንፈስ ቅዱስን ማታለላቸው፥ መዋሸታቸውና፥ መፈታተናቸው ነው። ይህም ያን ያህል ሸጠው ይህን ያህል ሸጥን ማለታቸውና ለማለትም መስማማታቸውና መመካከራቸው ነበር። በሌሎች ዘንድ ያልሆኑትን ለመሆን ሞከሩ። ይህን ያደረጉት በሰው ፊት ብቻ ሳይሆን በጌታም ፊት ነበር። ሰዎች ልብንና ኩላሊትን ስለማይፈትኑ ምንም ላይሉና ላያደርጉ ይችሉ ይሆናል። በቁጥር 3 እንደምናነበው ግን ጴጥሮስ ጌታ ገልጦለት ማታለላቸውን ብቻ ሳይሆን የአሳቡ ምንጭ ሰይጣን እንደሆነም ተረድቶ ነበር። መፈታተን የተሰኘው እዚህ ቦታ የተጠቀሰው ቃል ወደ መጥፎ መምራት ወይም ማሰናከል ማለት ነው። እነ ሐናንያ ይህን በማድረጋቸው እግዚአብሔር መጥፎ እንዲያደርግ ማለትም ኃጢአትን እንዲታገስና ሲያታልሉት እንዳላታለሉት እንዲቆጥር የሞከሩ ይመስላል። በዚህ ድርጊታቸው ሐናንያና ሰጲራ በስጋ ሞት ተቀጡ።

## 4. መንፈስ ቅዱስን ማሳዘን (ኤፌ.4:30)

"ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ።" የዚህን ጥቅስ ሙሉ ትርጓሜ ለማግኘት ከ25-32 ያለውን ምንባብ መመርመር ተገቢ ነው። እነዚህ ጥቅሶች በሙሉ ሁለት ቦታ የሚከፈሉ ክርስቲያናዊ ባህርያትን ያመለክታሉ። የመጀመሪያው ለአንድ ነገር የሚኖረን ድርጊታዊ አመለካከት ሲሆን ሁለተኛው የምንናገረውን ቃል የሚመለከት ነው። ውሸትን ማስወገድ፥ እውነትን መነጋገር፥ መቆጣት ግን ኃጢአትን ያለማድረግና ተቆጥቶ ውሎ ያለማደር፥ ያለመስረቅና እንዲያውም እየሰሩ ከሌላው ጋር መካፈል፥ የሚያንጽ በጎ ቃል እንጂ ክፉን ያለመናገር። እነዚህ ሁሉ ከዋናው ጥቅሳችን (ቁ.30) በፊት የተዘረዘሩ ሲሆኑ ከቁጥር 30 ቀጥሎ

ደግሞ መራርነትን፥ ንዴትን፥ ቁጣን፥ ጩኸትን፥ መሳደብን፥ ከክፋት ሁሉ ጋር ስለማስወገድ በማሳሰብ እርስ በርስ ቸርና ርህሩህ ስለመሆን፥ ጌታ እኛን ይቅር እንዳለ ይቅር ስለመባባል ይገልፃል። በነዚህ መካከል ነው መንፈስን እንዳናሳዝን የሚለው ቃል የተነገረው።

ከላይ የተዘረዘሩትን እንድናደርግና እንድንናገር የታዘዝናቸው ነገሮች ከሌሎች ሰዎች ጋር የሚኖረንን ግንኙነት የሚቀርጹ ነገሮች ናቸው። ከሌሎች ሰዎች ጋር የሚኖረን ግንኙነት ደግሞ የክርስትና ሕይወታችን የሚለካበት ሁለተኛው መንገድ ነው። ከሌሎች ሰዎች ጋር የሚኖረን ግንኙነት ጥሩ ሲሆን እግዚአብሔር ይከብራል፥ ግንኙነታችን መልካም እንዲሆን ደግሞ ይፈልጋል ይረዳናልም። ይህ ካልሆነ ግን እግዚአብሔር ያለመከበሩ ብቻ ሳይሆን እንዲያውም ሰይጣን እድል ፈንታ ያገኝና ሕይወታችንን ያነሳቁለዋል። እንዲህ ያለ ኑሮ ማለትም በውሸት፥ በቁጣ፥ በስርቆት፥ ክፉ ቃል በመናገር፥ በመራርነት፥ በንዴት፥ በጩኸት፥ በስድብና በክፋት፥ በጭካኔና ይቅር ባለማለት መኖራችን መንፈስ ቅዱስን ያሳዝነዋል።

በውስጣችን አንድ ኃጢአት ከኖረ መንፈስ ቅዱስ ያዝናል። መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ሲያዝን ሰላም አይኖረንም። አንድ ክርስቲያን ኃጢአት ከሰራ በኋላ ሕይወቱ እውነተኛ መናወጥ የሚናወጠው ለዚህ ነው። ይህ ረብሻና መናወጥ የእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ምልክት ነው። የተበላሸና ቶሎ ተብሎም መስተካከል ያለበት ነገር የመኖሩም ጠቋሚና ማስጠንቀቂያ ነው። ከዚህ በኋላ መወሰድ ያለበት እርምጃ ግልጽ ነው፤ ያም ጥፋትንና ኃጢአትን መረዳትና በ1ዮሐ.1:9 መሠረት የበደልን ሥርየት መጠየቅና የኃጢአት ይቅርታን መቀበል ነው። ጉዳዩ እግዚአብሔርን ብቻ የሚመለከት ከሆነ ንስሃ በመግባት ከእርሱ ዘንድ ይቅርታን ማግኘት ሌላ ሰውን የሚመለከት ከሆነ ደግሞ ሳይውሉና ሳያድሩ ወደዚያ ሰው መሄድና ችግርን መፍታት አስፈላጊ ነው። መንፈስ ቅዱስ ማዘኑ የማንነቱን ባህርይ ማለትም አካልነቱን የሚያስረዳን አንድ እውነት ነው። መንፈስ ቅዱስ የሚያዝን የሚደሰትም ስሜት ያለው አካል እንጂ ስሜት የለሽ የሆነ አንድ ኃይል አይደለም። እኛ ሰዎች ከሌሎች ሰዎች ጋር እንኳ በሚኖረን ግንኙነት ሌላው ሰው እንዳያዝንብን ወይም ምንም መጥፎ ስሜት እንዳይሰማው በጣም እንጠነቀቃለን። መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ በሚኖርበት ዘመን ሁሉ በምንም አያስከፋንም፤ አስከፍቶንም አያውቅም። እኛ ግን በብዙ መንገዶች ከአሳባችን አንስተን በአነጋገራችን አድርገን እስከ ድርጊታችን ባሉት ነገሮች ሁሉ መንፈስ ቅዱስን ልናሳዝነው እንችላለን። ስለዚህም አብዝተን ተጠንቃቂዎች ልንሆን ይገባናል። መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን የሚኖረው ቅዱስ አምላክ መሆኑን ከቶ አንዘንጋ። እርሱ በኛ ውስጥ ለዘላለም ሊኖር ወደኛ የመጣ ቅዱስ አምላክ ነውና ትቶን አይሄድም። ለኛ ጥቃቅን የሚመስሉን ኃጢአቶች እንኳ ከእርሱ ባህርይ ጋር ስለሚፃረሩ በኛ

ውስጥ የሚኖረው ትር..የሃዘን እንዳይሆንበትና..ለእርሱ.ም ቹ መኖሪያዎች ልንሆንለት ልንተጋ ያሻናል።

## 5. መንፈስ ቅዱስን ማክፋፋት (ዕብ.10:29)

የዚህ ጥቅስ አሳብ ከላይ ከፍ ብሎ የሚጀምር ነው። ጠቅላላ አሳቡ በምዕራፉ በሙሉ አለ ያለው ደግሞ ከ26-31 ባለው ክፍል ይገኛል። አሳቡም ካመኑ በኋላ ወደ ክህደት መመለስ የሚያስከትለውን ቅጣት ያመለክታል። በጥቅስ 29 ላይ ሦስት የአለማመን ወይም የክህደት ማለትም ከእምነት የመመለስ ውጤት የሆኑ ክሶች ተሰንዝረዋል። እነዚህም፤

- የእግዚአብሔርን ልጅ መርገጥ

- የተቀደሱበትን የኪዳን ደም እንደ ርኩስ መቁጠር

- የጸጋውን መንፈስ ማክፋፋት ናቸው።

በሦስተኛው ነጥብ የተጠቀሰው 'የጸጋ መንፈስ' የተባለው መንፈስ ቅዱስ ነው። አንዴ ሲያምኑ በውስጣቸው መኖር የጀመረውን ቅዱስ መንፈስ የሚያክፋፉትን ሰዎች እግዚአብሔር ይቀጣቸዋል። በዚህ ክፍል የተጠቀሰው ቅጣት ምን መሆኑ በግልጽ ባይነገርም ከፉ ነገር መሆኑ ግን ተወስቷል።

## 6. መንፈስን ማጥፋት (1ተሰ.5:19)

ይህ ጥቅስ "መንፈስን አታጥፉ" ብሎ ያዝዘናል። ይህንንም ከአውደ ንባቡ ጋር እንድንመለከተው ቢያንስ ከ 12 ጀምሮ መመልከት አስፈላጊ ነው። 1ተሰ.5 የመጀመሪያው ክፍል ስለ ጌታ ምጽአት ይናገርና የሚቀጥለው ክፍል ደግሞ በርካታ ምክሮች የታጨቁበት ምንባብ ነው። በዚህም ክፍል የተዘረዘሩ ብዙ ነጥቦች አሉ። መሪዎችን ማክበር፥ ያለ ስርዓት የሚሄዱትን መገሰጽ፥ ፈሪዎችን ማጽናናት፥ ለደካሞች መትጋት፥ ሰውን ሁሉ መታገስ፥ ለክፉ ክፉን ያለመመለስ፥ መልካሙን ለማድረግ መትጋት፥ ሁሌ ደስ መሰኘት፥ ሳያቋርጡ መጸለይ፥ በሁሉ ማመስገን፥ መንፈስን ያለማጥፋት፥ ትንቢትን ያለመናቅ፥ ሁሉን ፈትኖ መልካሙን መያዝ፥ ከማናቸውም ዓይነት ክፉ ነገር መራቅ ናቸው። አንድ ክርስቲያን ማድረግ ያለበት ትዕዛዝ ናቸው እኒህ። መንፈስን ያለማጥፋት ከነዚህ መካከል አንዱ ነው።

ማጥፋት የሚለው ቃል ልክ እሳትን በውሃ እንደማጥፋት የሚመስል ነው። መንፈስ ቅዱስ ከሚመሰልባቸው ምሳሌዎች መካከል አንዱ "እሳት" ነው። አንድ እሳት ከነደደ በኋላ በሁለት መንገዶች ይጠፋል። አንደኛው ዝም ማለት ሲሆን ሁለተኛው ሆን ብሎ ማጥፋት ነው። ሳይቋረጥ እንዲነድ ከተፈለገ ግን እንጨት በየጊዜው ሊማገድበት ያስፈልጋል። አንድ ክርስቲያንም ጌታን ሲቀበል በተጠመቀበትና በውስጡ ሊኖር በጀመረው መንፈስ ቅዱስ ዕለት ዕለት ካልተሞላ የመንፈስ ቅዱስ ስራ በሕይወቱ ቦግ ብሎ ሲነድድ አይታይም። ያ ሰው እየቆየ መንፈሳዊነቱ እየቀጨጨ ሲሄድ መታየቱ የማይቀር ነው። ሌላም አለ እሳት በውሃ ወይም በሌላ ነገር እንደሚጠፋ ወይም እየነደዱ ያሉት እንጨቶች ሲወገዱ እንደሚከስም የመንፈስ ቅዱስም ስራ ከአንድ አማኝ ውስጥ በተመሳሳይ ሁኔታ ሊጠፋ ይችላል። አንድ ክርስቲያን ኃጢአት ሲያደርግ መንፈስ ቅዱስ እንደሚያዝን ኃጢአት በማድረግ ሲኖር ወይም በግልጽ የጌታ ፈቃድ ያልሆነ ነገርን እያደረገ መኖር ሲቀጥል የመንፈስ ቅዱስ ስራ ከውስጡ ይጠፋል። እንዲህ ያለው ክርስቲያን በሕይወቱ ፈጽሞ ደስታና እርካታ አይሰማውም። የተጠራው በጌታ ሐሴት ለማድረግ ሲሆን እርሱ ግን ሁሌ በጨለማ እንደሚመላለስ ሆኖ ይኖራል። አንድ ክርስቲያን ከጨለማ ወደ ብርሃን ከመጣ በኋላ በብርሃኑ ብርሃንን እያየ መመላለስ ደግሞ ይኖርበታል። የመንፈስ ቅዱስም ስራ በውስጡ እየተንቀለቀለ እንዲበራ በየቀኑ በእርሱ መሞላት ይገባዋል።

መንፈስ ቅዱስ በዚህ ዘመን ኀልውናውን በኛ በአማኞች አድርጎ ሊያሳይ ከወደደ ይህ ለእኛ እጅግ ታላቅ ክብር ነው። ለዚህ ክብር ስለበቃን ከውስጣችን ሐሴት ልናደርግ እየተገባን ደግሞም ይህ ብርሃንና ሙቀት እርሱ የሚፈልገውን ያህል እንዲደምቅና እንዲዘምት ዕለት በዕለት በመንፈስ ቅዱስ የተሞላንና ለእርሱም አሰራር ምቹና ዝግጁ ልንሆን ያሻናል። በማቴ.25 እንዳሉት እንደ ልባሞቹ ቆነጃጅት ባለ ትርፍ ዘይቶችና ንቁ ጠባቂዎች ልንሆን ይገባናል።

መንፈስ ቅዱስን በተመለከተ ሊሰሩ የሚችሉና በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱ ኃጢአቶች እነዚህ ሲሆኑ የመጀመሪያዎቹን የማያምኑ ሰዎች የሚያደርጓቸው ናቸው። የኋለኞቹን ግን ክርስቲያኖች የሚሰሯቸው ኃጢአቶች ናቸውና አማኞች እኒህን ነገሮች ላለማድረግ መጠንቀቅ ይገባቸዋል። ዕለት ዕለትም ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የተቆራኘ ሕይወትን ለመኖር መትጋት ያሻቸዋል።